ካሳ ምን አለ 13

በማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል ስለ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ አንድ አረፍተ ነገር ድርጊትን ብቻ ሳይሆን፣ ሁነትንና ኹረትንም እንደሚያመለክት ገልፀን ነበር፡፡ በዚያም መሰረት እነዚህን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እንደሚከተለው አድርጎ በሁነትና በኹረት ግሶች አማካኝነት ማንሳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ካሳ የት አለ? 14
(ለ) ካሳ ምን ሆነ?

የመጀመሪያው የኹረት ሲሆን፣ ሁለተኛው የሁነት ጥያቄ ነው፡፡ መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም የገቡት ጥያቄውን ባለከተለው ተዋቃሪ ሀረግ ቦታ ላይ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ያየናቸው መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ነጠላ ጥያቄ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ይህም ማለት፣ አረፍተ ነገሮቹ የሚጠይቁት ስለ አንድ ነገር ወይም ድርጊት ወይም ኹረት ወይም ሁነት ብቻ ነው፡፡ መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም አንዳንድ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ አንዱ የጥያቄ አይነት ነው፡፡ ሌላው አይነት ድርብ ጥያቄዎችን የሚመለከት ነው፡፡ የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

(ሀ) ማን ምን አደረገ? 15
(ለ) ማን ከማን ጋር ምሳ በላ?
(መ) ማን ምን በላ?

የመጀመሪያው ምሳሌ ባለቤቱን ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጉን፣ ማለትም አድራጊውንና ድርጊቱን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አድራጊውን ከነአጋሩ የሚጠይቅ ነው፡፡ የመጨረሻው አድራጊውንና ተደራጊውን የሚመለከት ነው፡፡ እንደነዚህ ላሉ ድርብ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ድርብ ነው፡፡ ስለዚህም የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ፣

ካሳ እንጀራ በላ 16

የሚል አይነተ ይሆናል፡፡ የሌሎቹም መልስ በዚሁ ሁኔታ የሚሰጥ ነው፡፡

አንድ መጠይቅ አረፍተ ነገር ከድርብ አልፎ ድርብርብ ሲሆን ይችላል፡፡ ይህም በአንድ ጊዜ ከሁለት በላይ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ሊመለከት ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው፡፡

ማን ከማን ጋር ምን አደረገ? 17

ይህ አረፍተ ነገር አድራጊውን፣ አዳራጊውንና ድርጊቱን የሚመለከቱ መጠይቆችን ይዞአል፡፡ አድራጊውን **ማን**፣ በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም፣ አዳራጊውን ከማን ጋር በሚል ገላጭ መጠይቅ መሰተዋድዳዊ ሀረግ፣ እንደዚሁም ድርጊቱን ምን አደረገ? በሚል ግሳዊ ሀረግ በመጠየቅ ነው፡፡ ለእንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚሰጠው መልስም፣

ካሳ ከአናቱ ጋር ምሳ በላ 18

የሚል ይሆናል፡፡ አወቃቀሩ በተራ ቁጥር (16) የተገለፀው አይነት ነው፡፡ ርግጥ፣ እንደነዚህ ያሉ ድርብርብ ጥያቄዎች በአወቃቀር እንጅ በአጠቃቀም ላይ ላያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አብዛኛው የቋንቋዋው ተጠቃሚ የሚያተኩረው አንድን ነገር ብቻ በመግለፅ ወይም በመጠየቅ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ የቋንቋዋው ጥናት በሚባለው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሚታሰበውና ሊባል በሚችለው ጭምር የሚያተኩር በመሆኑ፣ የጥናቱን ትንተና በአብዛኛው ከአጠቃቀም ያለፈ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በአጠቃቀም ላይ ብቻ የሚወሰን ከሆነ፣ ብዙ ጥያቄዎች ያለምላሽ ይቀራሉ፡፡ የብዙዎቹ ጥያቄዎች መልስ ከሚባለው ሳይሆን፣ ከሚታሰበው፣ ማለትም አዕምሮአዊ ከሆነው የቋንቋዋ ችሎታ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ድርብም ሆነ ድርብርብ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም-ተከተላቸውን ሊያፋልሱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) ማን ምን በላ 19
(ለ) ማን ከማን ጋር ምን አደረገ?


እንጅ፣

(ሀ) ?ምን ማን በላ? 20
(ለ) ?ከማን ጋር ምን ማን አደረገ?

ማለት አይቻልም፡፡

ይህን የቅደም-ተከተል ገደብ ቀደም ሲል ከጠቀስነው ከሰዋዊነትና ከኢሰዋዊነት ባህሪ ጋር ማገናዘብ ይቻላል፡፡ ሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎች፣ ኢሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚገልፁ ሀረጎች የበለጠ አፅንዖትን ይፈልጋሉ፡፡ ይህን የሚያገኙት፣ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሲገኙ እንደሆነ ገልፀናል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎች፣ ሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ቀድመው በላዕላይ መዋቅር ሲገቡ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያጣል፡፡ የምሳሌ (20)ን ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

21




ምን የሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም ክፍት ከሆነው (...) ታሀታይ ቦታው ወጥቶ፣ ማን የሚለውን ለዋዊ ባለቤት መጠይቅ ተውላጠ ስም በመቅደምና ከፍ ካለ ርከን ላይ በመቀመጡ፣ ውጤቱ ተቀባይነት የሌለው መጠይቃዊ አረፍተ ነገር ሲሆን ችሎአል፡፡

እንግዲህ ስለ መጠይቅ አረፍተ ነገር እስካሁን በዝርዝር ያቀረብነውን እንደሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክር፡፡ መጠይቅ አረፍተ ነገር አንድ ነገርን ለማወቅ ወይም ለማረጋገጥ የሚነገር የአረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ መዋቅራዊ ባህሪው መጠይቅ ተውላጠ ስሞችን፣ መጠይቅ ምዕላዶችን ወይም ግሶችን በሚጠየቀው ሀረግ ቦታ ላይ ማስገባት ነው፡፡ ተውላጠ ስሞቹ ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ምዕላዶቹ ደግሞ እንዴ እና ወይ የሚሉት ናቸው፡፡ ግሶቹም አደረገና አለ ናቸው፡፡ የሚገልፁትም እንደ ቅደም-ተከተላቸው ድርጊትንና ብለትን ነው፡፡ በመጠይቅ ተውላጠ ስሞች አማካኝነት የሚጠየቁት አድራጊ፣ ተደራጊ፣ ገላጭና መስተዓምር ናቸው፡፡ አድራጊ፣ ተደራጊና መስተዓምር ስማዊ ሀረግ የሆነ መልስ ይፈልጋሉ፡፡ ገላጭ ጥያቄዎች ስማዊ ወይም መስተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ፡፡ የድርጊትና የሁነት ጥያቄዎች ግሳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ፡፡ ባጠቃላይ ጥያቄዎች በመጠይቅ ተውላጠ ስም፣ በመጠይቅ ተውላጠ ግስ፣ በቃለ ጥያቄና በቅላፄ መልክ ይከሰታሉ፡፡

ጥያቄዎች ነጠላ፣ ድርብና ድርብርብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነጠላ ጥያቄዎች አንድ ነገር ወይም ድርጊት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ አንድ የመጠይቅ ተውላጥ ብቻ ይሻሉ፡፡ ድርብ መጠይቆች በአንድ ጊዜ ሁለት ሀረጎችን የሚጠይቁ ሲሆኑ፣

ድርብርብ የሚባሉት ደግሞ ከሁለት በላይ የሆኑ ሀረጎችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ድርብም ሆኑ ድርብርብ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም ተከተላቸውን አይለቁም፡፡ በዚህም የመጠይቅ አረፍተ ነገሮችን ጉዳይ ለጊዜው አልባት ሰጥተን ወደሚቀጥለው ርዕስ ጉዳይ እንሄዳለን፡፡ ለጊዜው የምንልበት ምክንያት በሌላ ቦታ በሌላ አይነት መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ስለምንገናኝ ነው፡፡

## *አሉታዊ አረፍተ ነገር*

አንድ አረፍተ ነገር፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የሚያትት ወይም የሚጠይቅ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ የታተተውን የሚያልት (አሌ የሚል) ሊሆንም ይችላል፡፡ የሚያልተውም ቀደም ሲል በሀተታ አረፍተ ነገር የተገለፀን አንድ ሀሳብ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው አረፍተ ነገር አሉታዊ ይባላል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የምናተኩረው በእሉ ላይ ነው፡፡ የሚከተለውን ለአብነት እንመልከት፡፡

[ካሳ [ከእናቱ ጋር [ምሳውን በላ]]] 1


በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ስማዊ ሀረጎች፣ አንድ መስተዋድዳዊ ሀረግና አንድ ግሳዊ ሀረግ አሉ፡፡ የነዚህ ቅንጅት የሆነው አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ እንደ አንድ ሰፊ ሀረግ የሚቆጠር ነው፤ ለዚያውም ግሳዊ፡፡ የሀረጎቹ መዋቅራዊ ዝምድና በቅንፎቹ እንደተመለከተው ነው፡፡ መጀመሪያ ግሉና ምሳውን የሚለው ስማዊ ሀረግ [ምሳውን በላ] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ፡፡ ይህ ሀረግ ምሳ የመብላትን ፅንሰ-ሀሳብ ይገልፃል፡፡ ይህ ንዑስ ሀረግ [ከእናቱ ጋር] ከሚለው አዳራጊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ [ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ ሀረጉም ከእናት ጋር ምሳ የመብላትን ሀሳብ ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ይህን አቢይ ግሳዊ ሀረግ ካሳ ከሚለው አድራጊ ስማዊ ሀረግ ጋር በማቀናጀት፣ [ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን ሰፊ መዋቅር እናገኛለን፡፡ ይህም የአረፍተ ነገሩ መዋቅር ነው፡፡ ሀሳባዊ ይዘቱ የካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ የመብላቱ ድርጊት ነው፡፡ ይህ አረፍተ ነገራዊ ሀሳብ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙት ተዋቃሪ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ውጤት ነው፡፡ የሀረጎቹ ሀሳብም እንደዚሁ በውስጣቸው የሚገኙ ንዑስ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ አንድ አረፍተ ነገር የሚነገርበት ምክንያት አንድን ሙሉ ሀሳብ ለተነጋሪ ለማሳወቅ ወይም ለማስገንዘብ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ አረፍተ ነገሩ ሰዋሰዋዊ፣ ማለትም የመዋቅርን ህግ የጠበቀ፣ ሙሉ ሀሳብን ያዘለና ውነትን የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፤ ውነት አንፃራዊ

ቢሆንም፡፡ አንድ አረፍተ ነገር በቅርፁ የተስተካከለ፣ በይዘቱም የተሟላ ሆኖ ሳለ፣ ውነትን ግን በከፊልም ሆነ በሙሉ ላያንፀባርቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፤ ከላይ የተጠቀሰው አረፍተ ነገር የዚህ አይነት ሀፀፅ ካለበት፣ አድማጩ፣ ማለትም ተነጋሪው፣ ላይቀበለው ይችላል፡፡ ካልተቀበለው ደግሞ እንደሚከተለው አድርጎ <u>ሊያልተው</u> ይችሳል፡፡

ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ አልበላም 2

ይህ አረፍተ ነገር ከላይ ከተሰጠው አወንታዊ አቻው የሚለየው በግሱ ቅርፀ ነው፡፡ ግሱ /አል-/ የሚል መነሻና /-ም/ የሚል መድረሻ አለው፡፡ በዚህም ምክንያት አወንታዊ የነበረው አረፍተ ነገር ወደ አሉታዊነት ተለውጦአል፡፡ የአሉታዊነቱ መንለዔ /አል-/ የሚለው ምዕላድ ብቻ ነው፡፡ /-ም/ የተራ አሉታዊ አረፍተ ነገር ምልክት ወይም ሞይ ነች፡፡ ግንኙነትዋም ከተወሰነ ሀረግ ጋር ሳይሆን፣ ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ጋር ነው፡፡ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር፤ እንደ <u>ወይ</u> ወይም <u>እንዴ</u> ያለ ምዕላዳዊ ምልክት እንዳለው ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ተራ አወንታዊ የሀተታ አረፍተ ነገር ለአወንታዊነቱ የተለየ ምዕላዳዊ ምልክት ወይም ሞይ የሰውም፡፡ በዚህም ከሌሎቹ ይለያል፡፡ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተሰውን ይመስላል፡፡



3

/-ም/ ሞይ ለመሆንዋ ምልክቱ፣ አረፍተ ነገሩ ከሌላ አይነት ሞይ ጋር በሚቀርብበት ጊዜ አሰዋ በቦታዋ ላይ አለመገኘትዋ ነው፡፡ ሁለተኛም ከላይ እንደሚታየው /-ም/ ልትቀር ትችላለች፡፡ በመቅረትዋ ግን የአረፍተ ነገሩ አሉታዊነት አይቀየርም፡፡ ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡

[አስቴር [ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ እንዳልበላ (<u>እንደ</u> አል-በላ)] ታውቃለች] 4

ይህ ከሁለት አረፍተ ነገሮች የተዋቀረ ሰፊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ተዋቃሪዎቹ አረፍተ ነገሮች በውስጠኛውና በውጪኛው ቅንፎች ውስጥ የተመለከቱት ናቸው፡፡ በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ የሚገኘው አረፍተ ነገር አሉታዊ ነው፡፡ በመሆኑም የአሉታዊ ምዕላድ የሆነችውን /አል-/ን ብቻ በግሉ መነሻ ላይ ያሳያል፡፡ ይህ አረፍተ ነገር የውጪኛው አረፍተ ነገር ተጠጊ ነው፡፡ ለዚህ ጥገኝነቱ ምልክት እንድትሆነው <u>እንደ</u> የምትሰዋን ምዕላድ በግሉ ላይ ያሳያል፡፡ /-ም/ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ አትታይም፣ ልትታይም አትችልም፤ ምክንያቱም እሰዋ የተራ አሉታዊ አረፍተ ነገር ሞይ ነች፡፡

ወደ ምሳሌው እንመለስና የታሰተውን ሀሳብ ለማየት እንሞክር፡፡ በግልፅ እንደሚታየው፣ የእሌትዋ ምዕላድ የምትገኘው ከግሱ ጋር ስለሆነ፣ የታሰተው ሀሳብ በግሱ የተገለፀው ምሳ የመብላት ድርጊት ነው፣ ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ይህ አባባል ግን ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም እሌቱ በግሉ ላይ ብቻ ሳይወሰን፣ በእሉ መሪነት የተዋቀረውን አቢይ ግሳዊ ሀረግም ሊጨምር ይችላል፡፡ እንዲያውም ከዚያም አልፎ በከፊልም ቢሆን፣ ከዚሁ አቢይ ሀረግና ካሳ ከሚለው ስማዊ ሀረግ የተዋቀረውን አረፍተ ነገር ጭምር ሊጠቅስ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል፣ እሳቹ ምዕላድ በግሉ ላይ ይለጠፍ እንጅ፣ እሌቱ ከግሱ አልፎ ማንኛውንም ሀረግ ሊሸፍን ይችላል፡፡ ስለዚህም አረፍተ ነገሩ በቁሙ በጣም አሻሚ ነው፡፡ አሻሚነቱን እንደሚከተሰው እያደረጉ ማስወገድ ይቻላል፡፡

(ሀ) ከእናቱ ጋር ምሳ የበላው <u>ካሳ</u> አይደለም፤ አበበ ነው 5

(ለ) ካሳ ምሳ የበላው <u>ከእናቱ ጋር</u> አይደለም፤ ከእህቱ ጋር ነው


(መ) ካሳ ከእናቱ ጋር የበላው <u>ምሳ</u> አይደለም፤ ራት ነው

(ሰ) ካሳ ከእናቱ ጋር <u>ምሳ አልበላም</u>፤ <u>ጠሳ ጠጣ</u> እንጅ

በዚህ አይነት <u>ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ አልበላም</u> የሚለው አንድ አረፍተ ነገር ወደ አራት አረፍተ ነገሮች ሊተነተን ችሎአል፡፡ የትንተናው ሥላረት ትርጉም ሊሆን፣ የዚህም ምንጭ እሳቹ ምዕላድ ነው፡፡ ምዕላዱ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘውን ማንኛውንም ሀረግ ሊያልት ይችላል፡፡ ይህ ግን በትንተና የሚገኝ እንጅ ከአረፍተ ነገሩ ቅርፅ የሚታይ አይደለም፡፡ ምዕላዱ በግልፅ የሚታየው በግሱ ላይ ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ የምዕላዱ የዕሌት ሰፋት ወይም መጠን በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙትን ሀረጎች ሊያዳርስና በመጨረሻም ራሱን አረፍተ ነገሩን ሊሸፍን ይችላል፡፡ ከዚህም የዕሌት ዳር ድንበር ሊሰፋና ሊጠብ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል ሰለ መጠይቅ አረፍተ ነገር ስንወያይ፣ የመጠይቁ ምዕላድ መዋቅራዊ ግንኙነት ከአረፍተ ነገሩ ጋር እንደሆነ ገልፀን ነበር፡፡ በዚያው አካሄድ፣ የዕሌቱ ምዕላድ መዋቅራዊ ዝምድናም እንደዚሁ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህንንም በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

6





በግልፅ እንደሚታየው፣ የዕሌቱ ምዕላድ መዋቅራዊ ግንኙነት ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው፡፡ የዕሌቱን *መጠነ ሰፋት* ከግሱ ጀምሮ፣ ወደ ላይ በመውጣት ደረጃ በደረጃ እያሰፋ፣ እስከ አረፍተ ነገሩ መዋቅር ድረስ መሄድ ይቻላል፡፡ ጠባቡ የዕሌት መጠን አልበላም በሚለው ግስ ሲወሰን፣ ከፍተኛው ደግሞ ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም እስከሚለው አረፍተ ነገር ድረስ ይሄዳል፡፡ ከዚህም የምንረዳው፣ የአንድን አሉታዊ አረፍተ ነገር ፍች ከንበታዊ ቅርፁ በቀላሉ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ፍችው በማያሻማ ሁኔታ ሊታወቅ የሚችለው፣ አረፍተ ነገሩ የተነገረበት አውደ ነገር ሲታወቅ ነው፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ፣ አረፍተ ነገሩ በውስጡ ያለውን የሀረግ መጠን ያህል ፍችው የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህን የተለያየ አሉታዊ ፍች በሶስት መንገድ ማግኘት ይቻላል፡፡ አንደኛው ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ አይደለም በሚለው አሉታዊ የሁነት ግስ አማካኝነት እገሌ እንጅ፣ እገሌ አይደለም፤ በማለት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንዲታለት የተፈለገውን ሀረግ ከታሀታይ ቦታው እያነሱ፣ እሳቹ ምዕላድ ጋር እንዲዋቀር በማደረግ ነው፡፡

(ሀ) ከእናቱ ጋር ምሳውን [ካሳ አልበላም] 7
(ለ) ካሳ ምሳውን [ከእናቱ ጋር አልበላም]
(መ) ከእናቱ ጋር ካሳ [ምሳውን አልበላም]

በነዚሀ ምሳሌዎች ውስጥ፤ ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ እና ተሳቢው ስማዊ ሀረግ የዕሌቱ ምዕላድ ወዳለበት በመጠጋት ሊታለቱ ችለዋል፡፡ ሁኔታውን በዕፀ መዋቅር እንደሚከተሰው እናሳያለን፡፡



8

በግልፅ እንደሚታየው፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ በነጠብጣብ ከተመለከተው ታህታይ ቦታው፣ ማለትም ከግሳዊ ሀረጉ (ግሀ2) ውስጥ፣ ተነስቶ እላቹ ምዕላድ ወደሚገኝበት ወደ (እነ') በመሄድ ከምዕላዱ ጋር ተዋቅሮአል፡፡ በዚሁ አይነት ሌሎቹም ሀረጎች ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዱ ከልል ሲጠጉ እሌት ይሆናሉ፡፡ ግሱም እንደዚሁ ወደ እሌቱ ምዕላድ በመሄድ ይታለትና መጀመሪያ <u>እል-በላ</u> ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ይኸው ዕልት ግስ ወደ ዋይዋ ምዕላድ ይወጣና <u>አልበላም</u> ይሆናል፡፡ በዚህም ቦታውን ለቆ ከሄደው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ ይህም ማለት፣ ሁሉቱም ከግሳዊ ሀረጉ ወጥተው በእነ" ጥላ ስር ከእላቹ ምዕላድ ጋር ይገናኛሉ ማለት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ መዋቅራዊ የሆነው የእሌት ስርዓት ነው፡፡ ሌላው ንበታዊ ነው፡፡ ይህም ሊታለት የተፈለገውን ሀረግ ከሌሎቹ ለይቶ በጎላ ቅላጼ በመናገር ነው፡፡ ይህን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

(ሀ) ́ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም 9

(ለ) ካሳ ́ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም

(ሐ) ካሳ ከእናቱ ጋር ́ምሳውን አልበላም

እዝባሩ ያረፈባቸው ሀረጎች ደምቀው (ጎልተው) የሚነገሩት፣ እናም የሚታለቱት ናቸው፡፡

እስካሁን የተመለከትነው /እል-/ በሚለው የእሌት ምዕላድ አማካኝነት የሚገለፀውን እሌት ነው፡፡ እንዳየነውም ይህ ምዕላድ በግሀድ የሚታየው፣ በግሱ መነሻ ላይ ነው፡፡ ስለዚህም ግሳዊ የእሌት ምዕላድ ልንለው እንችላለን፡፡

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስማዊ እሌትን እንመስከታለን፡፡ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡፡

(ሀ) ብዙ ህፃናት ያለረዳት (የ-እለ-ረዳት) ያድጋሉ 10
(ለ) ብዙ ሰዎች ያለትዳር (የ-እለ-ትዳር) ይኖራሉ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>ያለረዳት</u> እና <u>ያለትዳር</u> የሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መስተዋድዱ /የ/ ነው፡፡ /እለ-/ የሚለው የስማዊ ሀረግ የእሌት ምዕላድ ነው፡፡ መዋቅራዊ ግንኙቱ ከስማዊ ሀረጉ ጋር ነው፡፡ /የ/ መስተዋድድ ስመሆንዋ ማስረጃው /ከ/ በሚለው መስተዋድድ ያለምንም የትርጉም ለውጥ ልትተካ መቻልዋ ነው፡፡ ይኸውም /ከ-እለ-ረዳት/ በምንልበት ጊዜ ነው፡፡ ሁለተኛም ሀረጉ እወንታዊ ሲሆን፣ መስተዋድዱ በቦታው ይገኛል፡፡ ይህ ሲሆን 10(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ብዙ ልጆች ቡ-ረዳት ያድጋሉ 11

<u>ቡ-ረዳት</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ሲታስት የ-እስ-ረዳት ወይም <u>እስ-ረዳት</u> ይሆናል። በእወንታዊው መስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ <u>ቡ</u> የነበረው መስተዋድድ፣ በአሉታዊው ሀረግ <u>የ</u> ይሆናል። ባለፈው ክፍል እንደጠቀስነው፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎች በስማዊ ሀረግ ውስጥ ሁሉም <u>የ</u> በሚል እቻ መስተዋድድ ይተካሉ።

የእሌቱ ምዕላድ የሚገኘው ከስማዊ ሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን እንመልከት፤

(ሀ) ያለነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ 12
(ለ) [የ- [እሉ- [የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ]]]

ምሳሌ 12(ሀ) ላዕላይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። ታህታይ አቀማመጡ በ12(ለ) እንደሚታየው ነው። መስተዋድዱ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ <u>የ</u> ነው። ከእሱ ጋር የተዋቀረው አሉታዊ ስማዊ ሀረግ ነው። የእሌቱ ምዕላድ መዋቅራዊ ዝምድና ከስማዊ ሀረጉ ጋር ነው። እገባቡ ደግሞ እንደ መስተዋድዱ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው።

ይሀ አንዱ አይነት አገባብ ነው። ሌላው አይነት ቀደም ሲል በግሳዊ እሌት ውስጥ እንዳየነው፣ የእሌቱ ምዕላድ ከሀረጉ መሪ ጋር የሚታይበት ነው። ይህን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት አለ-መሄድ 13

ይሀ አረፍተ ነገራዊ ይዘት ያለው የእልት (የታሰተ) ስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። የእልቱ ምዕላድ /አለ-/ የሚታየው የሀረጉ መሪ ከሆነው ከ<u>መሄድ</u> ጋር ነው። ይሁን እንጅ፣ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከእጠቃላዩ ሀረግ ጋር እንጅ ከመሪው ጋር ብቻ አይደለም። ይህም አገባብ በምሳሌ 12(ለ) ከሚታየው አገባብ ጋር የሚቃረን ይመስላል። በምሳሌ 12(ለ) ምዕላዱ ሀረጉን ቀድሞ ከመስተዋምሩ ጋር ይታያል። በዚህኛው ግን ከሀረጉ መሪ ጋር በሀረጉ መጨረሻ ላይ ይታያል። ጥያቄው ታዲያ፣ የእሌቱ ምዕላድ መሰረታዊ ቦታ የትኛው ነው? የሚል ነው።

በምሳሌ (12) የሚታየው የእሌቱ ምዕላድ አገባብ፣ በምሳሌ (7) እንደሚታየው ባለ ግሳዊ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚታይ አገባብ ነው። ከዚሁ እንፃር፣ የምሳሌ (13)ን እቻ ግሳዊ አረፍተ ነገር ብንመለከት፣ የሚከተለውን እንደሚመስል እንረዳለን።


እነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት አል-ሄዱም 14

በዚህና በምሳሌ (13) ውስጥ የሚታየው የእሌቱ ምዕላድ አገባብ አንድ አይነት ነው። ይሁን እንጅ፣ በምሳሌ (12) ከሚታየው አገባብ የተለየ ነው።

ከፍ ሲል የተነሳውን የእሌቱን ምዕላድ የመሰረታዊ አገባብ ጥያቄ በሁለት መንገድ መመለስ ይቻላል፡፡ አንደኛው፣ በግሀድ እንደሚታየው፣ መዋቅሮችን ለማዊና ግሳዊ ብሎ በመለየት የእሌቱን አገባብም ከዚሁ ልዩነት ጋር ማያያዝ ነው፡፡ መዋቅሩ ለማዊ ሲሆን፣ በመነሻ፤ መዋቅሩ ግሳዊ ሲሆን፣ በመድረሻ ላይ ይገባል ብሎ፣ ልዩነቱን መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ የእሌቱ ምዕላድ ሁለት ታህታይ አገባብ አለው እንደ ማለት ነው፡፡ ይህም የአገባቡን ስርዓት አጠቃላይነት ያሳጣዋል፡፡ አንድ መዋቅር ሲገኝ የሚችለው በመሰረቱ በአንድ ታህታይ ቦታ ብቻ ነው፡፡ ያን ታህታይ ቦታ አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ሊለቅና በሌላ ቦታ ገብቶ ሊታይ ይችላል፡፡

የእሌቱን ምዕላድ መሰረታዊ ቦታ ለመወሰን ሁለተኛው መንገድ፣ አጠቃላዩን የቋዋንቋዋውን የሀረግ አወቃቀር ስርዓት፣ ከመሪና ከተመሪ አቀማመጥ አኩዋያ ማየት ነው፡፡ ባለፈው ክፍል ስለ ሀረጎች ለንወያይ በሰፋት እንደ ተመለከትነው፣ ሀረጎቹ ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ መሪያቸውን አንዳንድ ጊዜ በግራ የሚያለቀምጡት መስተዋድዳዊና መስተዓምራዊ ሀረጎች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ይህንን የሚያደርጉት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ በሌሎቹ ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በሀረጉ መድረሻ ላይ ነው፡፡ አጠቃላይ ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ የማንኛውም ሀረግ ታህታይ አወቃቀር፣ መሪውን በቀኝ፣ ማለትም በመድረሻ፣ ላይ ያስቀምጣል፤ ብሎ ማጠቃለል እንደሚቻል ገልፀናል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ በተራ ቁጥር (12)ና (13) የሚታየውን የተሰያየ የእሌት ምዕላድ አገባብ እንደሚከተለው አድርጎ በአንድ ላይ ማቅረብ ይቻላል፡፡

15



እነዚህ በቅንፍ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች፣ አረፍተ ነገራዊ ይዘት ያላቸው ስማዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መሪዎቹ የተስመረባቸው ስሞች ናቸው፡፡ የሁለቱም ሀረጎች ታህታይ ቦታ ከአሊቱ ምዕላድና ከመስተዋድዱ በፊት ነው፡፡ በተራ ቁጥር 12(ለ) እና (13) የሚታየውን ላዕላይ ቅርፃቸውን የሚይዙት፣ ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዶቹ ቀኝ ጎን ሲሄዱ ነው፡፡ የሚሄዱበት ምክንያትም ለመታለት ነው፡፡ አካሄዳቸው እንደሚከተለው ነው፡፡ መጀመሪያ መሄድ የሚለው ስም ወደ አላቹ ምዕላድ ወደ /አለ-/ ይሄድና አለ-መሄድ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በተራው ወደ /የ-/ ይሄድና ከጎንዋ ሲለጠፍ የአለመሄድ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ፣ እነዚያ የሚለው /አለ-/ ወደሚለው አላች ይሄድና አለ-እነዚያ ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ አለእነዚያ የሚለው ወደ /የ-/ ይሄድና የ-አለእነዚያ ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ የሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ የሚለው ክፍል እንዳለ ይሄድና በቀኝ በኩል ይሰለፋል[8]፡፡

እስካሁን ያየነው የተራ አሊትን መዋቅራዊ ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን የድርብ አሊትን ስርዓት እንመለከታለን፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ ያለነብስ (የ-አለ-ነብስ) ጠላ አይጠጣም (አል-ይ-ጠጣም) 16


ይህ ተራ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ተራ የሚያሰኘው አንድ ግስ፣ ብሎም ግሳዊ ሀረግ፣ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ሁለት የአሊት ሀረጎችን ስለያዘ የአሊት ደረጃው ድርብ ነው፡፡ የገብስ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ /አለ-/ በሚለው ስማዊ የአሊት ምዕላድ፣ ጠጣ የሚለው ግስ ደግሞ /አል-/ በሚለው ግሳዊ የአሊት ምዕላድ ታልተዋል፡፡ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣

ካሳ ያለገብስ ጠላ ሌላ መጠጥ አይጠጣም 17

የሚል ነው፡፡ ሌላ መጠጥ የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ተሳቢነቱ ለአልቱ ግስ ነው፡፡ ያለገብስ ጠላ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ የዚህ ስማዊ ሀረግ አጎላማሽ ነው፡፡ የሁለቱን መዋቅራዊ ዝምድና እና የአረፍተ ነገሩን ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

[8] ዝርዝሩ ብዙ ነው፤ እንቅስቃሴውም በውነቱ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ለቀላል አቀራረብ ሲባል ግን በዚሁ እንወሰነዋለን፡፡ ወደፊት በሌላ ፅሁፍ የተለየና የበለጠ አጥጋቢ የሚመስል ትንተና እናቀርባለን፡፡ ለአሁኑ ይህን ውነት ብለን እንቀበል፤ ነገ ውሸት ሊሆን እንደሚችል ታማምነን፡፡ ውነት አንፃራዊ ነውና፤ የዛሬ ውነት፣ የነገ ውሸት ነው፡፡

18




በግልፅ እንደሚታየው፣ የገባስ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ /አስ-/ በሚለው ስማዊ
አላች ምዕላድ ታልቶአል፡፡ አልቱ ስማዊ ሀረግ /የ-/ ከሚለው መስተዋድድ ጋር
ተዋቅሮአል፡፡ ይህ አንደኛው አሌት ሲሆን፣ ሌላው፣ ካሳ ያለ ገባስ ጠላ ይጠጣ

የሚለው አረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህም የታሉተው /አል-/ በሚለው ግሳዊ የዕሴት ምዕላድ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ኢውሱን ተውላጠ ስሞችን ከስማዊና ከግሳዊ የአሉት ምዕላዶች ጋር በመጠቀም የአሉቱን ደረጃ ድርብርብ ማድረግ ይቻላል፡፡ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንም[9] | የትም | የማንም | አንድም | 19 |
| ምንም | መቼም | የምንም | | |

እነዚህ በሙሉ /-ም/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት ከየመጠይቁ ተውላጠ ስምና <u>አንድ</u> ከሚለው ኢውሱን ተውላጠ ስም የተመሰረቱ ናቸው፡፡ አገልግሎታቸው በመስተዓምርነት ነው፡፡ እነሱ የሚገቡበት አረፍተ ነገርም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ማንም ለማንም ምንም አይሰጥም (አል-ይ-ሰጥ-ም) 20
(ለ)* ማንም ለማንም ምንም ይሰጣል

የኢውሱን ተውላጠ ስሞቹ አገባብ በመስተዓምርነት ነው፡፡ የሚታመሩት ስማዊ ሀረጎች ማንነት ከአውደ ነገሩ ስለሚታወቅ፣ ሊገደፉ ይችላሉ፡፡ በሚገደፉበት ጊዜ አረፍተ ነገሮቹ ከላይ የሚታየውን ቅርፅ ይይዛሉ፡፡ በማይገደፉበት ጊዜ ደግሞ የአረፍተ ነገሮቹ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ማንም <u>ሰው</u> ለማንም <u>ሰው</u> ምንም <u>ነገር</u> አይሰጥም 21

ከምሳሌዎቹ የምንረዳው ሌላው ነገር፣ ግሳዊ ሀረጎቹ ከኢውሱናቹ ተውላጠ ስሞች ጋር በአሉት ስምሙ መሆናቸው ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ኢውሱናቹ ተውላጠ ስሞች በተፈጥሮአቸው አልት አይደሉም፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) ካሳ <u>ማንንም</u> ያምናል 22
(ለ) ካሳ <u>ማንንም</u> አያምንም

---

[9] እነዚህ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች አሻሚ ትርጉም አላቸው፡፡ ለምሳሌ፣ <u>ማንም</u> የሚለው በእንግሊዝኛው anyone ወይም no one የሚለውን ኢውሱን ተውላጠ ስም ሊተካ ይችላል፡፡ አሉት ግስ የሚፈልገው no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ ነው፡፡ anyone በሚለው ትርጉሙ ከአወንታዊ ግስ ጋር ሊዋቀር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣

ማንም ሊመጣ <u>ይችላል</u>

ማለት ይቻላል፡፡ no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ፣

ማንም ሊመጣ <u>አይችልም</u>

ይሆናል፡፡ <u>አንድ</u> የሚለው ምዕላድ እንደ እህዝ የአንድን ነገር መጠን ያመለክታል፡፡ እንደ ኢውሱን መስተዓምር ደግሞ የአንድን ነገር ዕምር ወይም ዕውቅ አለመሆን ያመለክታል፡፡ ስለዚህም አሻሚ ምዕላድ ነው፡፡

ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም እንደ ማንንም ያሉ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች ጥሬ ትርጉም አሻሚ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ አሉታዊነቱም ሆነ አወንታዊነቱ በግሱ ላይ የተመሰረተ ነው፣ (ማስታወሻ (9)ን ይመልከቱ፡፡) በዚህም ባህሪያቸው፣ /አስ-/ በሚለው የእሌት ምዕላድ አማካኝነት ከሚታሰቱት ሰማዊ ሀረጎች ይለያሉ፡፡

ግሳዊ ሀረጉ ከእነዚህ አይነት ተውላጠ ስሞች ጋር ሲዋቀር የግድ እሌት ይሆናል፡፡ ከሌሎች እሌት ሰማዊ ሀረጎች ጋር ሲዋቀር ግን፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ እሌት ላይሆን ይችላል፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

ካሳ ያስተዳር ብዙ ጊዜ ኖሮአል 23

ይህም በእሌት ሰማዊ ሀረጎችና በኢውሱን ተውላጠ ስሞች መካከል ያወቃቀር ልዩነት እንዳለ ያሳያል፡፡ ይህ ልዩነት ግን በተራ አረፍተ ነገር ደረጃ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ ውስብስብ ሲሆን፣ ግሱ እሌት ላይሆን ይችላል፡፡ ይህን ከሚከተለው መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል 24
(ለ) ማንም ወደ እኔ ላይመጣ ይችላል
(ሐ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ ይችላል
(መ) ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም

ኢውሱን ተውላጠ ስሞች በጥሬ ነገራቸው አሻሚ የሆኑትን ያህል፣ የማያሻማ እሌት ትርጉም ያለው አንድ ቃል አለ፡፡ እሱም ቀረ የሚለው ግስ ነው፡፡ ይህ ግስ የሚገኝበት አረፍተ ነገር ሁሉ እሌት ነው፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ልጆቹ መጥተው ቀሩ 25
(ለ) ነጋዴው ከሰሮ ቀረ

እነዚህ ውስብስብ አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ውስብስብ ያደረጋቸው ሁለት ግሶችን በውስጣቸው መያዛቸው ነው፡፡ አሉታዊ ያደረጋቸው ደግሞ ቀረ የሚለው ግስ /አል-/ የሚለውን የእሌት ምዕላድ በያዘ ሌላ ግስ ሊተካ መቻሉ ነው፡፡ ይህ ሲሆን አረፍተ ነገሮቹ እንደሚከተለው ይሆናሉ፡፡

(ሀ) ልጆቹ አልተመለሱም 26
(ለ) ነጋዴው አላተረፈም

ቀረ የሚለው ግስ /አል-/ በሚለው የዕሌት ምዕላድ እንደገና ሊታሰት ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ትርጉሙ አሉታዊ ሳይሆን አወንታዊ ነው፡፡

ልጆቹ ወጥተው አልቀሩም 27

የዚህ አረፍተ ነገር ትርጉም ልጆቹ ተመልሰዋል የሚል ነው፡፡

ከፍ ሲል ኢውሉን ተውላጠ ስሞች ከአሉት ግስ ጋር እንደሚዋቀሩ ገልፀን ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ቀረ ከሚለው እሌት ግስ ጋር አይዋቀሩም፡፡ የሚዋቀሩት አል-ቀረ ከሚለው ድርብ እሌት ግስ ጋር ነው፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

(ሀ) *ማንም ለምሳ ቀረ 28
(ለ) ማንም ለምሳ አልቀረም

የምሳሌ (ሀ) ተቀባይነት ማጣት የሚያሳየው፣ የኢውሉኖቹ ተውላጠ ሰሞች ስምሙነት በተፈጥሮው እሌት ከሆነ ግስ ጋር ሳይሆን፣ በ/አል-/ አማካኝነት ከታለተ ግስ ጋር እንደሆነ የሚያሳይ ይመስላል፡፡

እስካሁን የተመለከትነው ህገኛ ሊባል የሚችለውን የእሌት ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ለየት የሚለው የሁነትና የኑረት ግሶች ባህሪ ነው፡፡ ግሶቹ እሌትን የሚያሳዩት በ/አል-/ አማካኝነት ሳይሆን፣ ቅርፃቸውን በመለወጥ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ጎበዝ ነው 29
(ለ) ካሳ ጎበዝ አይደለም
(መ) *ካሳ ጎበዝ አልነውም

ነው የሚለው የሁነት ግስ ነው፡፡ አሉታዊ ቅርፁ አይደለም እንጅ፣ አልነውም አይደለም፡፡ አልነውም የሚለው ቅርፅ ለምን ተቀባይነትን ሊያጣ ቻለ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ወደ መልሱ ከመሄዳችን በፊት የኑረት ግስን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ቤት ውስጥ አለ 30
(ለ) ካሳ ቤት ውስጥ የለም
(መ) *ካሳ ቤት ውስጥ አል-አለ-ም

ነው የሚለው የሁነት ግስ ከድርጊትም ሆነ ከባህሪ ግሶች የተለየ ነው፡፡ የሚለየውም በቅርፁና ከዚህም ጋር በሚያያዘው በርባታ ደረጃው ነው፡፡ ቅርፁ /ን-/ በሚለው አንድ ተናባቢ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም ከሶስት ተናባቢዎች ከሚመሰረቱ ሌሎች ግሶች ይለያል፡፡ ሁለተኛም /ን-/ ምንም ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም የሚያገኘው እሱን ተከትለው ከሚገቡ የርባታ ምዕላዶች ብቻ ነው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው፤ የባለቤት አይደሉም፡፡ የተሳቢ አፀፋ የሚታየው በመሰረቱ በሳቢ ግስ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት /ን-/ የርባታ ምዕላድ ለመሸከም ብቻ የሚገባ ትርጉም-የለሽ ቅርፅ ወይም ምዕላድ እንጅ፣ ግስ አይደለም ለማለት ይቻላል፡፡ ምናልባትም የርባታ ምዕላዶቹ የተሳቢ አፀፋ የሆኑት ምዕላዱ መደበኛ ባለትርጉም ግስ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡

የለም የሚለው እልት ግስ መሰረት አለ የሚለው የኑረት ግስ ነው፡፡ የአሉት ምዕላዱ የግዕሁ /ኢ-/ እንጅ የአማርኛው /አል-/ አይደለም የሚሉ አሉ፡፡ ስለዚህም ታህታይ ቅርፁ /ኢ-አለ-ም/ ሲሆን፣ /ኢ-/ ወደ /ይ-/ ትለወጥና፣ ቅርፁ /ይ-አለ-ም/ የሚል ይሆናል፡፡ ጉዳዩ *በይነ-ልሳናዊ* የሆነ ጠለቅ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ፡ እዚህ ላይ የምንጨምረው የለም፡፡ በጥቅሉ የኑረትና የሁነት ግሶች ስርዓት ከሌሎቹ የተለየ ነው፡ ብለን እናልፈዋለን፡፡

## *ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች*

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተቱት አረፍተ ነገሮች ሀተታን የሚያትቱ፣ ጥያቄን የሚጠይቁ ወይም ሀሳብን የሚያልቱ ሳይሆኑ፣ ትእዛዝን የሚሰጡ ናቸው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ትዕዛዝ እንቀፅ በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ የትዕዛዝን በር የሚያሳዩ እንደማለት ነው፡፡ እኛ ግን ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ልንላቸው እንችላለን፡፡ ትዕዛዝን የሚያሳዩት አረፍተ ነገራዊ ቅርፅና ይዘት ያላቸው የመዋቅር አይነት ናቸውና፡፡ ይሁኑ እንጅ፣ ከሌሎቹ አረፍተ ነገሮች የሚለዩበት ባህሪያት ስላሉዋቸው፡ እነሱን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመረምራለን፡፡

መዋቅራዊ ባህሪያቸው የተወሰነ፣ ማለትም የታመረ ባለቤት የሚፈልጉ መሆናቸው ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ባለቤታቸው ማንኛውም እምር ስማዊ ሀረግ ሳይሆን፣ በዋናነት የሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ብቻ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ጠጅ አምጣ! 1
(ለ) ወጥ አውጪ!

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ባለቤት አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ሲሆን፣ የሁለተኛው ደግሞ አንቺ የሚለው እንስታይ ተውላጠ ስም ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛውና ዋናው ስዋሰዋዊ ሲሆን፣ ከዚሁ ላይ የሚመሰረተውና ሁለተኛው ማስረጃ ንግግራዊ ነው፡፡ ሰዋሰዋዊውን በሚመለከት፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደሚከተለው ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

(ሀ) አንተ ጠጅ አምጣ! 2
(ለ) አንቺ ወጥ አውጪ /አውጥ-ኢ/

ከላይ ያለባለቤት የሚታዩት አረፍተ ነገሮች እዚህ ላይ ከነባለቤታቸው ይታያሉ፡፡ ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ መሆኑ በግሀድ ይታያል፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛው ምሳሌ ግስ መድረሻ ላይ የምትገኘው /-ኢ/፣ በክፍል ሁለት ስለፆታ ስንወያይ እንደገለፅነው፣ የሁለተኛ መደብ እንስታይ ፆታ ምዕላድ ነች፡፡

እነዚህ እንግዲህ ሰዋሰዋዊ ማስረጃ ያልናቸው ሲሆኑ፣ ንግግራዊ ማስረጃ የምንለው ደግሞ እነዚህን አረፍተ ነገሮች በሚናገረውና በሚነገረው ሰው መካከል

ባለው ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች አንድ ተናጋሪ ካጠገቡ ለሚገኝ አንድ ሌላ ሰው በትዕዛዛዊ ቅላጼ የሚነገሩ ናቸው፡፡ ካሁን በፊት እንደገለፅነው፣ ተናጋሪው አንደኛ መደብ ይባላል፤ ንግግር ጀማሪ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተነጋሪው ሁለተኛ መደብ ይባላል፤ የነገሩ መድረሻ ነው፡፡ ተናጋሪንና ተነጋሪን የሚታዘብ ሌላ ሰው ካለ፣ ያ ሰው ሶስተኛ መደብ እንደሚባል ቀደም ሲል ተገልፆአል፡፡ ከዚህ ንግግራዊ አውድ አኩዋያ ሲታይ፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባለቤት ሁለተኛ መደብ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በአረፍተ ነገር ላይ በግሀድ የማይታየውም ለዚህ ነው፣ ዕውቅ ለለሆነ፡፡

የማይገደፈው በአፅንዖት ሲነገር ብቻ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ተው! 3
(ለ) አንተ ተው!

የመጀመሪያው መደበኛ ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን መደበኛ ብቻ ሳይሆን፣ ማስጠንቀቂያም ጭምር ነው፡፡ 'ተው ይህ ነገር አያዋጣህም' የሚል አይነት ነው፡፡ ስለዚህም አስጠንቃቂ ትዕዛዝ ልንለው እንችላለን፡፡ ከዚህ ካለፈም አረፍተ ነገሩ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፡፡

(አንተ) ተው ብየሃለሁ! 4

ይህ ትዕግስቱን የጨረሰ ሰው የሚናገረው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ከትዕዛዝ ደረጃ ያለፈ የዛቻ አነጋገር ነው፡፡

ሁኔታው ትዕዛዝ የተለያየ ተግባር፣ አይነትና ደረጃ እንዳለውና፣ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችም በዚሁ ላይ የሚመሰረት የተለያየ ቅርፅ ሲኖራቸው እንደሚችሉ ያሳያል[10]፡፡ እሁንም የሚከተሉትን እናነፃፅር፡፡

(ሀ) ልብሱን እጠቡ-ው /-ኡ/ 5
(ለ) ልብሉን እጠብ
(መ) ልብስ እጠብ

ከነዚህ ምሳሌዎች መካከል የሚታይ የቅርፅ ልዩነት አለ፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ዕምር ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው፡፡ የዚሁ ሀረግ አፀፋ የሆነችው /-ኡ/ም በግሱ መድረሻ ላይ ትታያለች፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ግን እፀፋዋ አትታይም፡፡ በሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ ዕምር አይደለም፡፡ ስላልሆነም በግሱ ላይ በአፀፋ አልተጠቀሰም፡፡ ከነዚህ የቅርፅ ልዩነቶች የመነጨ የሚመስል የትዕዛዝ ልዩነትም ያለ ይመስላል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ምሳሌ ለስለስ ያለ ትዕዛዝን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከዚህ ከረር ያለ ትዕዛዝን

[10] በዚህ ጉዳይ ላይ ሀይሉ (1980)ን ይመልከቱ፡፡

የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ሶስተኛው ከሁሉም የበለጠ የትዕዛዝ መንፈስ ያለበት ይመስላል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ዕምርነት የመደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባህሪ ያለመሆኑን ነው፡፡ ዕምር ሰማዊ ሀረግ ያለበት ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ከትዕዛዛዊነት ይልቅ ወደ ማሳሳቢያነት የሚያዘነብል ይመስላል፡፡

የሚከተሰውን ደግሞ እንመልከት፡፡

(ሀ) ብላ! 6
(ለ) በል ብላ!
(መ) በል ብላት!

አንድ ምግብ አልበላም እያለ የሚያስቸግርን ልጅ ብናስብ፣ የእነዚህን ምሳሌዎች አግባብነት በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ተራ ትዕዛዝ ነው፡፡ ሁለተኛው ወላጅ ከልጁ አጠገብ ቁሞ ከዛቻ ጋር የሚሰጠው ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሶስተኛው ከዛቻ ያለፈ ሀይል የሚታይበት ትዕዛዝ ነው፡፡ ልጁ አንድም እየተመታ፣ አለያም ከተመታ በሁዋላ ምግቡን እያለቀሰ የሚበላበት ሁኔታ ነው፡፡ በሶስተኛው ምሳሌ መጨረሻ ላይ የምትታየው /-አት/ ይህን ሁኔታ የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ በቅርፅዋ የሶለተኛ መደብ እንስታይ ፆታ፣ የተሳቢ አፀፋ ትመስላለች፡፡ ግን አይደለችም፡፡ ብትሆን ኖሮ፣ በሳቢ ግስ ላይ ብቻ ትገኝ ነበር፡፡ የሚከተሰውን እንመልከት፡፡

(ሀ) በል ተኛት 7
(ለ) በል ሂዳት

<u>ተኛ</u> እና <u>ሂድ</u> የሚሉት ኢሳቢ ግሶች ስለሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋ ሊይዙ አይችሉም፡፡ ለለዚህም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ /-አት/ በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተሳቢ አፀፋ ሳትሆን፣ የዱላ ቀረሽ ትዕዛዝ ምልክት ነች፡፡ የዛቻ ምዕላድ ልንላት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ልጅ አልታዘዝም ብሎ አየሮጠ ቢሄድ፣ ከአዛዡ በኩል፣

(ሀ) ቆይ ትመጣለህ! 8

ወይም

(ለ) ቆይ ትመጣታለህ! (ት-መጥ-አት-አለህ)

የሚል ዛቻ ይደርሰበታል፡፡ የመጀመሪያው ተራ ዛቻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከዚያ የከፋ ነው፡፡ /-አት/ ም የምትገኘው በዚሁ በሁለተኛው ምሳሌ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር የሚነገረው አዛዥ ወይም ገሳጭ በሆነ ቅላፄ ነው፡፡ በመደበኛ የንግግር ቅላፄ ከተነገረ፣ ትዕዛዛዊ መሆኑ ይቀርና ፈቃጅ፣ ጋባዥ ወይም ተለማማጭ ይሆናል፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ጠጣ 9
(ለ) በል ጠጣ
(ሐ) በል ጠጣት
(ሰ) ትጠጣት

ቅላፄአቸው ካልታወቀ በስተቀር፣ እንደነዚህ ያሉ አባባሎችን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ በማየት ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ትዕዛዛዊ የሚሆኑት፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ በትዕዛዛዊ ቅላፄ ሲነገሩ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውጭ ፈቃድን፣ ግብዣን፣ ቁልምጫን፣ ወዘተ፣ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አኳር ሲታይ፣ የመጀመሪያው ምሳሌ፣ 'ጠላ ልጠጣ?' ብሎ ለሚጠይቅ ልጅ የሚሰጥ ፈቃድ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አልጠጣም እያለ ለሚግደረደር ተጋባዥ የሚነገር የግብዣ አነጋገር ሊሆን ይችላል፡፡ ሶስተኛው፣ 'ጠጣ እንጅ! ይቺ ደግሞ ምን አላት?' እያለ የሚጋብዝ ወይም የሚያባብል ነው፡፡ የመጨረሻውም ተጋባዥ በትዕዛዝ ሳይሆን፣ በፈቃደኛነት እንዲጠጣ የሚጠይቅ ነው፡፡ ቅርፁም የካልዓይ አንቀፅ ነው፡፡

ሁኔታው አረፍተ ነገሮችን በሚታዩበት መልካቸው ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው፣ ለማለት እንደማይቻል ያስገነዝባል፡፡ ትዕዛዛዊነታቸው በውል የሚታወቀው፣ ሲታዩ ሳይሆን፣ ሲባሉና በጆሮ ሲሰሙ ብቻ ነው፡፡ ባጭሩ ትዕዛዛዊነት መዋቅራዊ ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ጭምር ነው፡፡

እስካሁን ያየነው አንድ ሰው አንድን ሌላ ሰው ሊያዝ የሚጠቀምበትን የአረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ ትዕዛዙ አዛዥና ታዛዥ ፊት-ለፊት ሲገናኙ የሚሰጥ ነው፡፡ ከዚህ ለየት የሚለው ትዕዛዝ ደግሞ አዛዥ ትዕዛዙን ለታዛዡ ፊት-ለፊት ሳይሆን፣ በመልክተኛ፣ ማለትም በሶስተኛ ሰው በኩል የሚያስተላልፍበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

(ሀ) ልብስ ትጠብ 10
(ለ) እንጨት ትሰበር
(ሐ) እንጀራ ትጋግር

እንደነዚህ ያሉት ኢርቱዕ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አንድን ትዕዛዝ በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ የሚያስተላልፉ ናቸውና፡፡ ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ ሳይሆን፣ ሶስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ከነባለቤታቸው እንደሚከተለው ሆነው ሊነገሩ ይቻላሉ፡፡


(ሀ) አስቴር ልብስ ትጠብ 11
(ለ) እያልነሽ እንጨት ትሰበር

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ትዕዛዝን ብቻ ሳይሆን፣ ፈቃድንም ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ‘አስቴር ወደ ትምህርት ቤት ትሂድ ወይ?’ ተብሎ ቢጠየቅና፣

ትሂድ 12

ቢል፣ መልሱ የፈቃድ አንጅ፣ የትዕዛዝ አይሆንም፡፡ ይህም የሚያመለክተው፣ ቀደም ሲል እንደተነገረው፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነሮችን የአሻሚነት ባሀሪ ነው፡፡ ትዕዛዝን ወይም ፈቃድን ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ ከሁለቱ የትኛውን እንደሚያመለክቱ በውል የሚታወቀው በሚነገሩበት ቅላፄ ብቻ ነው፡፡ የትዕዛዝ ቅላፄ ከፈቃድ፣ ከመጠይቅ፣ ከአሌት እንዲሁም ከሀተታ ቅላፄ የተለየ ነው[11]፡፡ እንደዚያም ሆኖ፣ መዋቅራዊ ቅርፁን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

13




በዚህ ክፍል ለንወያይ የቆየነው ስለ ተራ አረፍተ ነገሮች ያወቃቀር ስርዓትና ተግባር ነው፡፡ ተራ አረፍተ ነገሮች አንድ ግሳዊ ሀረግ ብቻ ያላቸው ናቸው፡፡ ተግባራቸው ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ አሉታዊና ትዕዛዛዊ ነው፡፡ የአንዱ አወቃቀር ከሌላው የተለየ ባህሪ አለው፡፡ በሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሁነትን፣ የኑረትን፣ የገቢርና የተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መዋቅራዊ ባህሪ አይተናል፡፡

የገቢር አረፍተ ነገር ባለቤት አድራጊ ወይም ገባሪ እንደሆነና ተገባሪ ስማዊ ሀረግ ሲኖረው እንደሚችል ገልፀናል፡፡ የተገብሮ አረፍተ ነገሮች ግስ ሳቢ የሆነ እቻ ግስ እንዳለውና ባለቤቱም ተደራጊ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ አይተናል፡፡ የተገብሮነት ምልክት የሆነችው ምዕላድም /ተ-/ እንደሆነችና እሰዋም በጥቅሉ _ማዕከላይ_ ድርጊትን ከምታመለክተው ከሌላዋ /ተ-/ በአገባብዋ የተለየች እንደሆነች ገልፀናል፡፡ በጥቅሉ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብሎ በመክፈል፣ የድርጊቶቹን ደግሞ ገቢር፣ ማዕካላይና ተገብሮ ብሎ መለየት እንደሚቻል ተገንዝበናል፡፡ በመጠይቅ አረፍተ ነገር ውስጥ የተራን፣ የድርብንና የድርብርብ መጠይቅን መዋቅራዊ ሁኔታ ተመልክተናል፡፡ የመጠይቅ ምዕላዶች _እንዴና_ _ወይ_ እንደሆኑ፣ መጠይቅ ተውላጠ ስሞችም ለጥያቄ መነሻ በሚሆነው ሀረግ መሰረታዊ ቦታ ላይ እንደሚገቡ አይተናል፡፡ ጥያቄዎቹ ተራ ድርብና ድርብርብ ሲሆኑ እንደሚችሉም ተገንዝበናል፡፡ አሉታዊ አረፍተ ነገሮችም /አል-/ እና /አለ-/ በሚሉት ምዕላዶች አማካኝነት እንደሚመሰረቱ አይተናል፡፡ በአይነታቸውም ተራ፣ ድርብና ድርብርብ አሌትን ሊያሳዩ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችን በሚመለከት በግስ ቅርፅ፣ በባለቤት ባህሪና በቅላፄ ሊለዩ እንደሚችሉ ተገንዝበናል፡፡ ከመዋቅር አልፈን እስከ ትርጉም ድረስ በመሄድ የተግባራቸውን አሻሚነትና ይህንንም አሻሚነት ለመፍታት ቅላፄ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልፀናል፡፡ በሁሉም አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግ አፀፋውን በግሱ አምድ ላይ የግድ ማሳየት እንዳለበትና በታህታይ መዋቅር ውስጥም ከሁሉም ሀረጎች ቀድሞና ከፍ ብሎ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ገልፀናል፡፡ ተሳቢ ስማዊ ሀረግም ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ ሊሆን እንደሚችልና በግሱ ላይም ከባለቤቱ አፀፋ ቀጥሎ በራሱ አፀፋ ሊጠቀስ እንደሚችል አይተናል፡፡ መስተዋድዳዊ ሀረጎችም እንደዚሁ በግሱ ላይ /ለ-/ ወይም /በ-/ በሚል መስተዋድድና በተሳቢ አፀፋ ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ተረድተናል፡፡ ግሱ ሊይዝ የሚችለው የባለቤትን፣ የርቱዕን እና የኢርቱዕን ወይም የመስተዋድድ ሀረግን አፀፋ ብቻ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ በዚህም የተራ አረፍተ ነገሮችን ውይይት አንቋጫለን፡፡

## መልመጃ

1. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ትንታኔ በዕፀ-መዋቅር ያመልክቱ፡፡

   (ሀ) ልጁ አስቴርን በጣም ተቀየማት፡፡
   (ለ) ልጁ ተገረፈ፡፡

---

[11] ዝርዝሩን ከዓለማየሁ (1988) ይመልከቱ

2. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተቀባይነት ሰምን አጠራጣሪ እንደሆነ ምክንያቱን ይግለፁ፡፡ ተቀባይነት እንዲያገኙ አድርገው ያዋቅሩአቸው፡፡

(ሀ) ? እሾህ እሰቴርን ወጋት፡፡
(ለ) ? ገነት አስቴርን ወስደችባት

3. የሚከተለውን አረፍተ ነገር ተንትነው በዕፀ-መዋቅር ያሳዩ፡፡

ልጆቹ ምሳ አልበሉም እንዴ?

4. "እንኩዋን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሰሀ" የሚለው አረፍተ ነገር ተግባር ምን እንደሆነ ይግለፁ፡፡ የዚህን አረፍተ ነገር ባሰቤት ይግለፁ፡፡

5. የአንድን አረፍተ ነገር ባለቤት ያለጥርጠር ማወቅ የሚቻለው በሰነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ፡፡

6. "ከዚህ ጥፋ!" የሚለው መዋቅር ተግባር ምንድን ነው፡፡ ባለቤቱ በምን ይታወቃል፡፡

7. የሚከተሉት መዋቅሮች ትርጉም አንድ አይነት ነው፡፡ ቅርፃቸው ለምን እንደተለያየ ያስረዱ፡፡

(ሀ) የካሳ መፅሀፍ ንባብ
(ሰ) ካሳ መፅሀፍ አነበበ
(መ) ካሳ መፅሀፍ ማንበቡ

8. ልጆቹን ጉንፋን ያዛቸው የሚሰው ሁተታዊ አረፍተ ነገር ባሰቤት ማን ነው? እንዴት?

9. አይነተኛ የተገብሮ ምዕላድ መለያ ምንድን ነው?

10. ካሳን ደከመው በሚሰው አረፍተ ነገርና ካሳ ደከመ በሚሰው አረፍተ ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዱ፡፡

# ውስብስብ አረፍተ ነገር

## *ውስብስብ ሀተታዊ አረፍተ ነገር*

ባለፈው ክፍል ስለተራ አረፍተ ነገሮች አይነት፣ ሰርዓትና ተግባር ተወያይተናል። ተራ አረፍተ ነገሮች ከተራ ስማዊና ግሳዊ ሀረግ ይዋቀራሉ። ተራ ሀረጎች ደግሞ ከተራ መሪ፣ ከሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽና መስተዓምር ይዋቀራሉ። ዝርዝር ሁኔታውን ቀደም ሲል ስለተለያዩ ሀረጎች ሰንወያይ ተመልክተነዋል። ለምሳሌ፣ አንድ ሳቢ ግስ ከመሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረትን አንደሚፈጥር፣ ያ ንዑስ ሀረግ ደግሞ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተቀናጅቶ አቢይ ሀረትን አንደሚመሰርት፣ አቢይ ሀረትም ከተለያዩ መሰተዓምሮች ጋር በመዋቀር ዋናውን አቢይ ሀረግ አንደሚያዋቅር አይተናል። በዚህ ሁኔታ የሚፈጠር ሀረግ ተራ ሀረግ ሲባል፣ ከዚህ አይነት ሀረግ የሚፈጠር አረፍተ ነገርም አንደዚሁ ተራ አረፍተ ነገር ይባላል። ተግባሩም ተራ ሀሳብን መግለፅ፣ መጠየቅ፣ ማለት (አሌ ማለት)፣ ወዘተ፣ ነው።

አንድ አረፍተ ነገር ተራ ካልሆነ ውስብሰብ ነው። አንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ደግሞ ከውስብሰብ ሀረጎች የሚፈጠር ሰፊ መዋቅር ነው። ውሰብሰብ ሀረጎች በውስጣቸው ተራ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ አረፍተ ነገራዊ የሆነ መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ አላቸው። አረፍተ ነገራዊው መሙሊያ ወይም አጎላማሽ ከግሳዊ ወይም ከሰማዊ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀር፣ ከዚህ አይነት ግሳዊ ወይም ሰማዊ ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም አንደዚሁ ውሰብሰብ ይሆናል። ተግባሩም አንደዚያው።

የዚህ አይነት ግሳዊና ስማዊ ሀረጎች ያሉዋቸውን አረፍተ ነገሮች ሰርዓት ከዚህ ቀጥሰን አንድ በአንድ እንመረምራለን። ከዚያ በፊት ግን በሀረግ ውሰጥ ሰለሚገኙ አረፍተ ነገሮች አንድ ነገር ማንሳት አለብን። ይኸውም አረፍተ ነገሮቹ ግሳዊና ስማዊ ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ነው። ግሳዊ የሚባሉት ግሳዊ ሀረግ ያላቸው ሲሆኑ፣ ሰማዊ የሚባሉት ደግሞ በግሳዊ ሀረግ ፋንታ ሰማዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን።

(ሀ) አሰቴር [በሩን ከፈተችው] (ከፈተ-ች-ው) 1
(ለ) አስቴር [በሩን መክፈትዋ] (መክፈት-ኡ-ኣ)
(መ) የአስቴር [በሩን መክፈት]
(ሰ) --------- [በሩን መክፈት]

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ ግሳዊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጉ በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ሲሆን፣ የዚህ ሀረግ መሪ ደግሞ [ከፈተ-ች-ው] የሚለው ሳቢ ግስ ነው፡፡ ግሱ የባለቤቱንና የተሳቢውን አፀፋ ያሳያል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ [በሩን መከፈትዋ] የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የሀረጉ መሪ [መከፈትዋ] የሚለው የድርጊት ስም ነው፡፡ እርዕሰት እንደሚባል በምስረታው ንዑስ ክፍል ተገልፆአል፡፡ ይህም መሪ [-ዋ ] < /ኡ-ኣ/ የምትለዋን ድርብ ምዕላድ አስከትሎአል፡፡ ይህች ምዕላድ በግሱ ላይ ከምትታየው የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ[-ች] < /-ት-ኢ/፣ ጋር በግብር አንድ ነች፡፡ ባለቤትን ትጠቁማለችና፡፡ በሁለቱ አፀፋዎች መካከል ያለው ልዩነት የቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት የመጣው አፀፋዎቹ ከተቀጠሉባቸው ቃላት ክፍል ልዩነት ነው፡፡ ቃላቱ ግሳዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ች] ትሆናለች፡፡ ቃላቱ ስማዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ዋ] ትሆናለች፡፡ ሁለተኛም ግሳዊ አረፍተ ነገር የባለቤትን ብቻ ሳይሆን፣ የተሳቢ አፀፋንም ሊያሳይ ይችላል፡፡ በአንፃሩ ስማዊ አረፍተ ነገር የተሳቢ አፀፋን አያሳይም፡፡ ከዚያም አልፎ ከምሳሌ (መ) እንደምንረዳው የባለቤት አፀፋንም ላያሳይ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ባለቤቱ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ በመነሻው ላይ ያሳያል፤ አለያም በምሳሌ (ረ) እንደሚታየው በግሀድ ከመታየት ይታቀባል፡፡

በአጠቃላይ በአፀፋ የሚጠቀስ ሀረግ በግሀድ ላይከሰት ይችላል፡፡ ከአፀፋው ቅርፅ የየሀረጉን መደብ፣ ቁጥር ወይም ፆታ ለማወቅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ ምሳሌ 1(ሀ) እና (ለ)ን እንደሚከተለው ለማለት ይቻላል፡፡

(ሀ) ----- [----- ከፈተችው] (ከፈተ-ች-ው) 2
(ለ) ----- [በሩን መከፈትዋ] (መከፈት-ዋ)

በምሳሌ (ሀ) የባለቤቱና የተሳቢው ሀረግ፣ በምሳሌ (ለ) የባለቤቱ ሀረግ ብቻ ተገድፈዋል፡፡ ስለ ስማዊና ግሳዊ አረፍተ ነገር ይህን ያህል ካልን፣ አሁን አረፍተ ነገሮቹ ወደሚገኙባቸው ሀረጎች እንመለስና መዋቅራዊ ባሀሪያቸውን እንይ፡፡ ከስማዊ ሀረጎች እንጀምራለን፡፡

## ውስብስብ ስማዊ ሀረግ

ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች በውስጣቸው መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ አረፍተ ነገር አላቸው፡፡ የሁለቱንም ዓይነት አረፍተ ነገሮች አገባብ ከዚህ ቀጥለን በየተራ እንመለከታለን፡፡


### (ሀ) መሙሊያ አረፍተ ነገር

መሙሊያ አረፍተ ነገሮች የሚባሉት፣ በአንድ ስማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ከመሪው ስም ጋር እየተዋቀሩ ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሚመሰርቱና የመሪውን ስም ይዘትም ሙሉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

[[የካሳ ቤት የመስራት] ዓላማ] 3

ይህ ስማዊ ሀረግ ነው። የሀረጉ መሪ [ዓላማ] የሚለው ስም ነው። ይህ መሪ [የካሳ ቤት የመስራት] ከሚለው መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ [የካሳ ቤት የመስራት ዓላማ] የሚል ሰፊ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል።

[የካሳ ቤት የመስራት] የሚለው መዋቅር ስማዊ አረፍተ ነገር ነው። አገባቡም ዓላማ ለሚለው መሪ ስም መሙሊያ ሆኖ ነው። ያለ መሙሊያው መሪው ስም ብቻ ሙሉ ሀሳብ አይሰጥም። የምን ዓላማ? የሚል አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል። ጥያቄው እንዳይነሳ ከፈለግን፣ የዓላማውን ይዘት መግለፅ ይኖርብናል። ይዘቱ የሚገለፀው በአረፍተ ነገር ስለሆነ፣ አረፍተ ነገሩ የመሪው ስም መሙሊያ ነው። ከመሪው ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ነው።




4

በግልፅ እንደሚታየው፣ [የካሳ ቤት የመስራት] የሚለው ስማዊ አረፍተ ነገር ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) አንጉዋ በመውረድ ዓላማ ከሚለው መሪ ስም ቀድሞ ገብቶአል፡፡ ይህ የመሙለያዎች አይነተኛ አገባብ ነው፡፡ ግንኙነታቸው በቀጥታ ከመሪው ስም ጋር ነው፡፡


መሙሊያው አረፍተ ነገር የካሳ ከሚለው ባለቤትና ቤት መስራት ከሚለው ስማዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፡፡ የካሳ በሚለው ስም መነሻ ላይ የምትታየው /የ/ ካሳ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት መሆኑን የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ አፀፋ ግን አይደለችም፡፡ ያለእሰዋ ካሳ የሚሰው ስም ባለቤት መሆኑ አይታወቅም፡፡ ምክንያቱም መስራት በሚለው መሪ ስም ላይ ካሳን የሚጠቁም አፀፋ የለምና፡፡ በአፀፋ ያልተጠቀሰ የስማዊ አረፍተ ነገር ባለቤት፣ እንድም ከላይ እንደሚታየው /የ/ን ያስቀድማል፣ አለያም ከቦታው ይጠፋል፡፡ ከላይ የሚታየው ሁኔታ ባለቤቱ /የ/ን አስቀድሞ በግሀድ ሲከሰት የሚያሳይ ነው፡፡ /የ/ን ባለማስቀደሙ ከቦታው ሲጠፋ ደግሞ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[--- ቤት መስራት] 5

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ መስራት የሚለው መሪ ላይ በአፀፋ ስላልተጠቀሰ፣ ማንነቱ አይታወቅም፡፡ ማንነቱ ስንል፣ መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው ማለታችን ነው፡፡

ሌላው ልንገነዘበው የሚገባ ነገር [ቤት የመስራት] በሚለው ሀረግ ውስጥ፣ መስራት በሚለው መሪ ስም መነሻ ላይ የምትታየውን /የ/ን ይመለከታል፡፡ ይህች /የ/ ስማዊ አረፍተ ነገሩ ነፃ ሳይሆን፣ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ ጥገኝነቱም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ዓላማ ለሚለው ለስማዊ ሀረጉ መሪ ነው፡፡ ስለዚህም ቀደም ሲል ካየናት ባለቤት አመልካች /የ/ በተግባርም ሆነ በአገባብ ትለያለች፡፡ ይህችኛዋ /የ/ ጥገኝነትን አመልካች ስትሆን፣ ያችኛዋ /የ/ ባለቤትነትን አመልካች ነች፡፡ ይህችኛዋ /የ/ በሳዕላይ መዋቅር ውስጥ፣ ከአረፍተ ነገሩ መሪ ስም ቀድማ ስትገባ፣ ያችኛዋ /የ/ ከአረፍተ ነገሩ ባለቤት ቀድማ ትገባለች፡፡ የዚችኛዋ /የ/ መሰረታዊ አገባብ ጥገኛ ከሆነው አረፍተ ነገር ጋር ነው፡፡ ጥገኛው አረፍተ ነገር በሞይነት የገባ መሆኑን ስለምታመለክት ምይ ልንላት ችለናል፡፡ አረፍተ ነገሩንም ተሞይ ልንለው እንችላለን፡፡ መሙሊያው የጥገኛው አረፍተ ነገርና የሞይዋ ቅንጅት ሲሆን፣ አቀነጃጀቱንም እንደሚከተለው በዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡

6




ይህ እንግዲህ የመመሲያው አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ ጥገኛ ሆኖ በመመሲያነት የገባ መሆኑን ከምታሳየው ከ/የ/ ጋር የተዋቀረ ስለሆነ፣ ይዘቱ ከመደበኛ፣ ማለትም ጥገኛ ካልሆነ፣ አረፍተ ነገር ይዘት የሰፋ ነው፡፡ ይህን ሰፊ መዋቅር (አነ') በሚል *ምህፃር* እናመለክታለን፡፡ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ሲተነተን፣ ከላይ እንደሚታየው፣ አረፍተ ነገር (አነ) እና ሞይ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ የሞዩ ቦታ በግልፅ እንደሚታየው ከመመሲያው አረፍተ ነገር በስተቀኝ ነው፡፡ /የ/ <u>መስራት</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር የሚቀናጀው በላዕላይ መዋቅር፣ ማለትም በንግግር ደረጃ ነው፡፡ /የ/ ራስዋን ችላ መቆም የማትችል ምዕላድ ስለሆነች፣ ደጋፊ ያስፈልጋታል፡፡ ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ደረጃ፣ አጠገብዋ ከሚገኘው፣ መስራት ከሚለው መሪ ስም መነሻ ላይ ልትለጠፍ ችላለች፡፡ ይህን ስታደርግም መስራት የነበረው መሪ ስም ቅርፁን ለውጦ <u>የመስራት</u> ይሆናል፡፡ ካሁን በፊት፣ በእሉታዊ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ግሱ ወደ እሌቱ ምዕላድ ሲሄድ አይተን ነበር፡፡ የአሁኑም <u>መስራት</u> የሚለው መሪ እካሄድ እንደዚያው አይነት መሆኑን እናስተውል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም የሞይዋ ታህታይ ቦታ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ስመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ሁለት ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛው ትውረታዊ ነው፡፡ ሞዮች የአረፍተ ነገር መሪ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ አንድ አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በእነሱ አማካኝነት ነውና፡፡ አንድ መሪ ግሳዊ፣ ስማዊ፣ ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ መሆኑ የሚታወቀው፣ መሪው ግስ፣ ስም፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ሲሆን እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በጥገኝነት ምልክቱ ነው፡፡ ይህም ሞዩ ነው፡፡ ቀደም ሲል በየደረጃው ያየናቸው ሀረጎች፣ መሪያቸው የሚገኘው መመሊያውን እየተከተለ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ሀረጎቹ በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት፣ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን መሪው፣ ማለትም ሞዩ፣ የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን በማለትም ቋንቋዋው በሀረግም ሆነ በአረፍተ ነገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመሪ አገባብ እንዳለው ለማሳየት ይቻላል፡፡ ይኸውም ቋንቋዋው ቀኝ መሪ ነው፣ የሚል አጠቃላይ መግለጫ በመስጠት ነው፡፡

ሁለተኛው ማስረጃ ትውረታዊ ብቻ ሳይሆን፣ ምክንያታዊ ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም እንደሚከተለው ያሉ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች መኖር ነው፡፡

(ሀ) ካሳ ሰራ ይሰራ ዘንድ 7

(ለ) አስቴር ምሳዋን ትበላ ዘንድ

በቀደምት ሊቃውንት፣ እንደነዚህ ያሉ መዋቅሮች ዘንድ አንቀፅ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አንደኛ <u>ዘንድ</u> የሚለውን ቃል ማስከተላቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው እንዲፈፀምልን የምንሻውን ድርጊት የሚገልፁ መሆናቸው ነው፡፡ "....ይፈፀምልኝ ዘንድ በትህትና አመለከታለሁ፣" እንደምንለው ማለት ነው፡፡

ውስጣዊ ይዘታቸው፣ አረፍተ ነገራዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ቅርፁ የመደበኛ ሳይሆን፣ የጥገኛ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ምልክቱ <u>ዘንድ</u> የሚለው ሞይ ነው፡፡ እሱም የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ በሰተቀኝ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት፣ በሌሎቹም ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሞዩ ቦታ እንደዚሁ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ዘንድ እንደ /የ/ ጥገኛ ሳይሆን፣ ራሱን የቻለ ምዕላድ ነው፡፡ ስለሆነም ካጠገቡ ከሚገኘው ግሰ ወይም ስም ላይ መጠጋት አያስፈልገውም፡፡ እንደ /የ/ ያሉ ሞዮች የሚለጠፉበት ምክንያት አቅመ ቢስ ድሁር እናም ምርኩዝ ፈላጊ መሆናቸው ነው[1]፡፡

[1] በዚህ ጉዳይ ላይ ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ፡፡ ምክንያቱ አቅመ-ቢስነት ላይሆን ይችላል፡፡ ወደ ውስብስብ ትውረት ስለሚወስደን ዝርዝር ውስጥ አንገባም፡፡

ይህ እንግዲህ የመሙሊያ አረፍተ ነገሮችንና የሞዮችን ቅንጅት በማመለከት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከአጎላማሽ አረፍተ ነገር ጋር ስለሚዋቀሩ ስማዊ ሀረጎች እንወያያለን፡፡

## (ለ) አዛማጅ አረፍተ ነገር

አዛማጅ አረፍተ ነገሮች[2] የሚባሉት አንድን ስማዊ ሀረግ በውስጣቸው ከሚገኝ ከማንኛውም ስማዊ ወይም መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር በማጣቀስ ይህኑ ስማዊ ሀረግ እየገለፁ የሚያጎላምሱ ውሱን መዋቅሮች ናቸው፡፡ የሚከተለው የእነዚህ ምሳሌ ነው፡፡

[ካሳ የሸጠው [የብራና መፅሀፍ]] 1

ይህ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ መሪው መፅሀፍ የሚለው ስም ነው፡፡ ይህ መሪ ስም የብራና ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ የብራና የሚለው ስማዊ ሀረግ፣ መፅሀፉ ከምን እንደተሰራ የሚያመለከት መሙሊያ ነው፡፡ መሪውና መሙሊያው የፈጠሩት ንዑስ ስማዊ ሀረግ [ካሳ የሸጠው] ከሚለው ገላጭ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ [ካሳ የሸጠው የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ውስብስብ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡

[ካሳ የሸጠው] 2


የሚለው መዋቅር ጥገኛ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል የጥገኝነት ምልክት ነች፣ ያልናትን /የ/ን ከግሱ ላይ ለጥፎአል፡፡ አረፍተ ነገሩ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ የካሳ ቤት የመሰራት እንደሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር፣ ስማዊ ሳይሆን፣ ግሳዊ ነው፡፡ ስለሆነም በግሱ መድረሻ ላይ፣ የባለቤትና የተሳቢ አፀፋዎችን አስከትሎአል፡፡ ስለዚህም ውሱን ነው፡፡ ባለቤቱ በአፀፋ ስለተጠቀሰ፣ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ አላስቀደመም፡፡

አረፍተ ነገሩ ጥገኛ ይሁን እንጅ፣ የብራና መፅሀፍ ለሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ አይደለም፤ አጎላማሽ ነው፡፡ የመሪው ስም መሙሊያው ከላይ እንደተገለፀው፣ የብራና የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ በአጎላማሽነቱ [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ ይገልፃል፡፡ እንደማንኛውም

[2] ስለ አዛማጅ አረፍተ ነገር ሀይሉ (1972)ን ይመልከቱ፡፡

እንላማሽ፣ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ይህን እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

3




ከዕፀ መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ ጥገኛው አረፍተ ነገር (አነ') የንዑሱ ስማዊ ሀረግ ገላጭ ሆኖ ገብቶአል፡፡ አወራረዱ ከእቢዩ ስማዊ ሀረግ ስሀ(2) እንጉዋ ላይ ነው፡፡ ይህ አይነተኛ የገላጭ ሀረጎች መዋቅራዊ ባህሪ ነው፡፡

አረፍተ ነገሩ (አነ) ከሞዩ ማሰትም ከ(/የ/) ጋር ተዋቅሮ ስሬውን ጥገኛ አረፍተ ነገር (አነ') መሰርቶአል፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ሞዩ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ይገኛል፡፡ አረፍተ ነገሩ ደግሞ፣ እንደ ማንኛውም ገላጭ

³በዚህ ምልክት (ᵢ) የሚጣቀሱ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡

አረፍተ ነገር፣ ከስማዊ ሀረግ ባለቤትና ከግሳዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፡፡ የግሳዊ ሀረጉ መሪ ሸጠ የሚለው ሳቢ ግስ ነው፡፡ ስለሆነም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው፡፡ ይሁን እንጅ፡ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ ቦታው ግን በሰረዝ (--) የተመለከተው ነው፡፡ በግሱ መድረሻ ላይ ይህንኑ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ የሚጠቁም አፀፋ አለ፡፡ እሱም /-እ/ ነው፡፡ ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን ያመለክታል፡፡ እንደዚህ ያለ ስማዊ ሀረግ ግን በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በግሀድ የለም፡፡ ስለዚህም ሸጠው የሚለው ግስ ተሳቢ ማነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡

ተሳቢው በግሀድ የማይታይ፣ ነገር ግን መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው የሚታወቅ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ሊታወቅ የቻለውም በግሱ ላይ ከሚታየው /-እ/ ከሚለው አፀፋ ነው፡፡ ይህ አፀፋ በግሱ ላይ የግድ መታየት አለበት፡፡ ካልታየ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ ይዘት ሊታወቅ አይችልም፣ እናም አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በሌላ አነጋገር፣

*[ካሳ የሸጠ] 4

ማለት አይቻልም፡፡

ሌላው ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፣ በአፀፋ የተጠቀሰ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ሁል ጊዜ በግሀድ አይታይም፣ ማለት ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ በርግጥ እንደዚህ ያለ ሀረግ በግሀድ ሊታይም ላይታይም ይችላል፡፡ ወሳኙ ሀረጉ የሚገኝበት የመዋቅር አይነት ነው፡፡ መዋቅሩ ከፍ ሲል እንደሚታየው ያለ ጥገኛ አረፍተ ነገር ከሆነ፣ ሀረጉ በአፀፋ ይጠቆማል እንጅ፣ በግሀድ ሊታይ አይችልም፡፡ መዋቅሩ ቀደም ሲል እንዳየነው ያለ ስማዊ አረፍተ ነገር ወይም ከዚህ በታች እንደሚታየው ያለ መደበኛ (ጥገኛ ያልሆነ) ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ በግሀድ ሊታይ ይችላል፡፡ ስለዚህም በተሳቢ አፀፋ ላይጠቀስ ይችላል፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ የብራና መፅሀፍ ሸጠ 5

እነሆ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ይታያል፡፡ በግሱ ላይም እሱን የሚጠቁም አፀፋ የለም፡፡

ከፍ ሲል በጥገኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ ሲጠቀስ እንጅ በግሀድ ሲከሰት እንደማይችል ገልፀናል፡፡ ከዚህም ላይ ለምን በግሀድ አይታይም? የሚል ጥያቄ አሁንም ይነሳ ይሆናል፡፡ ሀረጉ በግሀድ የማይታየው፣ በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ሀረጉ በአፀፋ በመጠቀሱና ከዚሁም ይዘቱ የሚታወቅ በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ይኸው ሀረግ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር በይዘት (ትርጉም) አንድ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ሀረግ የሚጠቁሙት አንድ ነገርን ነው፡፡ የማይታየው ተሳቢ ስማዊ ሀረግም [የብራና መፅሀፍ] የሚል ነው፡፡ ይህ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ቢወጣ፣

*[[ካሳ የብራና መፅሀፍ የሸጠው] የብራና መፅሀፍ] 6

የሚል ይሆናል፡፡ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ሀረግ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በተሳቢነት፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ ደግሞ በመሪነት ስለተከሰተ፣ ድግግሞሽን አስከትሎአል፡፡ ይህ አይነት ድግግሞሽም ከቋንቋዋ ባህሪ ጋር ይፃረራል፡፡ ቋንቋዋ አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽን ፈፅሞ አይፈቅድም፡፡ አዕምሮም እንደዚሁ፡፡ ለዚህ ነው፣ ሀረጉ ተቀባይነት የሌለው፡፡ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ከሁለቱ ተደጋጋሚ ስማዊ ሀረጎች አንደኛው የግድ በግሀድ እንዳይወጣ መታገድ ይኖርበታል፡፡ እንደዚህ የሚደረገው ደግሞ ማንኛውም ሳይሆን፣ በአፀፋ የሚጠቆመው ስማዊ ሀረግ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ይዘቱ ከአፀፋው አይነት ይታወቃልና፡፡ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይዘት /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ ስለሚታወቅ፣ በግሀድ እንዳይወጣ ታግዶአል፡፡

ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የትርጉም ብቻ ሳይሆን፣ የመዋቅርም ዝምድና አላቸው፡፡ ዝምድናውም ተሳቢውን ስማዊ ሀረግ የያዘው አረፍተ ነገር [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ስማዊ ሀረግ አጎላማሽ ሆኖ መግባቱ ነው፡፡ በአጎላማሽነቱም [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ በውስጡ ካለው ድብቅ ተሳቢ ጋር አዛምዶታል፡፡ የትኛው [የብራና መፅሀፍ] ብለን ብንጠይቅ፣ መልሱ [ካሳ የሸጠው] የሚል ይሆናል፡፡ ከዚህም ሁለቱን ስማዊ ሀረጎች የማዛመድ ተግባሩ የተነሳ፣ እንደ [ካሳ የሸጠው] ያለ መዋቅር አዛማጅ አረፍተ ነገር ይባላል፡፡

ይህ አይነቱ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል ካየነው መሙሲያ አረፍተ ነገር የተለየ ነው፡፡ ልዩነቱ በሶስት ወገን ነው፡፡ በአንድ ወገን፣ ይኸኛው አረፍተ ነገር፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ግሳዊ ነው፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከመሪው ስም ጋር ሳይሆን፣ ከንዑሱ ሀረግ ጋር ነው፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በውስጡ ያለውን በአፀፋ ብቻ የተጠቆመ ድብቅ ስማዊ ሀረግ አብሮት ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ስለሚያዛምድ፣ ገላጭና አዛማጅ ነው፤ መሙሲያ አይደለም፡፡

በአንድ አዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘን ድብቅ ስማዊ ሀረግ ተዛማጅ እንለዋለን፡፡ የሚዛመደውም በአረፍተ ነገሩ ከሚጎላመሰው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ከላይ በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ ተሳቢው ነው፡፡ ተዛማጅነት ግን የተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ የተለየ ባህሪ አይደለም፡፡ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግም ሊዛመድ ይችላል፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡


[--- አስቴርን የሰደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/) ልጆች] 7

ይህም፣ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (1) እንዳየነው መዋቅር፣ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ መሪው ልጆች የሚለው ስም ሲሆን፣ አጎላማሹ፣

[--- አስቴርን የሰደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/)] 8

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ አስቴርን የሰደቡአት የሚል ግላዊ ሀረግና በግሀድ የማይታይ ባለቤት ስማዊ ሀረግ አለው፡፡ ከግሱ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ፣ ባለቤቱ ሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር መሆኑን ለማወቅ ይቻላል፡፡ አዛማጁ አረፍተ ነገር ይህን ድብቅ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ልጆቹ ከሚለው ከዋናው ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ጋር አዛምዶታል፡፡ ስላዛመደውም ሀረጉ በግሀድ ከመታየት ታግዶአል፡፡ በግሀድ ቢታይ ኖሮ፣ መዋቅሩ [ልጆች አስቴርን የሰደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/) ልጆች] የሚል ይሆን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽ ያሳያልና፡፡ የአዛማጁን አረፍተ ነገርና የስማዊ ሀረጉን መዋቅራዊ ተዛምዶ አሁንም በዕፀ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

9




ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ ቦታው በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ ክፍት የሆነበት ምክንያት ሀረጉ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ስለተጠቀሰና ልጆቹ ከሚለው መሪ ስም ጋር

በትርጉም አንድ ሆኖ ስለተዛመደ ነው፡፡ ያዘማመዱም ሁኔታ ከፍ ሲል ካየነው የተሳቢ ስማዊ ሀረግ አዘማመድ ጋር አንድ ነው፡፡

እስካሁን ያየነው የአንድ አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤት ወይም ተሳቢ፣ በአረፍተ ነገሩ ከሚጎላመሰው ስማዊ ሀረግ ጋር የሚፈጥረውን መዋቅራዊ ዝምድና ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የተዛማጅ መስተዋድዳዊ ሀረግን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡


[[ልጆቹ የሂዱበት] ሀገር] 10

ይህ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ መሪው <u>ሀገር</u> የሚለው ስም ነው፡፡ አጎላማሹ፣

[ልጆቹ የሂዱበት] 11

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የዚህን አረፍተ ነገር ግስ ስንመለከት፣ /-ኡ/ እና /-በት/ የሚሉትን ቅጥያዎች እንዳስከተለ እንረዳለን፡፡ የመጀመሪያው ቅጣይ፣ <u>ልጆቹ</u> የሚለውን የብዙ ቁጥር ባለቤት የሚጠቁም፣ የብዙ ቁጥር አፀፋ ነው፡፡ ሁለተኛውስ? ሁለተኛው የሚጠቁመው አንድ በግሀድ የማይታይን መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ ሀረጉ መስተዋድዳዊ ለመሆኑ ከግሱ ባህሪ ማወቅ ይቻላል፡፡ <u>ሄደ</u> የሚለው ግስ መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግን በመሙሊያነት ይፈልጋል፡፡ የእንደዚህ አይነት መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪም <u>ወደ</u> ነው፡፡ ሀረጉ በግሀድ የማይታይበት ምክንያት፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ራሱ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግ በአፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ አፀፋውም /-በት/ ነው፡፡ ይህ አፀፋ ግን ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው፡፡ የ/በ/ እና የ/ት/ ቅንጅት ነው፡፡ /በ/ <u>ወደ</u> የሚለውን መስተዋድድ ሲወክል፣ /ት/ ከመስተዋድዱ ጋር የተዋቀረውን ስማዊ ሀረግ ትወክላለች፡፡ /-በት/ የሚለውን ውስብስብ የመስተዋድድ አፀፋ ልንለው እንችላለን፡፡ ውስብስብ ወይም ድርብ አፀፋዎችን ካሁን ቀደምም እንዳየን ያስታውሱ፡፡ ለምሳሌ፣ በስማዊ አረፍተ ነገር ውስጥ [-ዋ] የ/ኡ/ እና የ/ኣ/ ውሁድ፣ በግሳዊ አረፍተ ነገር ውስጥም [-ች] የ/-ት/ እና የ/-እ/ ውሁድ እንደሆነች አይተናል፡፡ ከዚህ ላይ የሚታየው /በት/ የሚለው አፀፋ አካሄድም እንደዚሁ ነው፡፡ የመዋቅሩን ተዛምዶ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናመለከታለን፡፡

12




እነሆ፣ የግሱ መሙሊያ የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (—) ነው፡፡ ክፍት የሆነበት ምክንያትም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ሀገር ከሚለው ከስማዊ ሀረጉ መሪ ጋር በአረፍተ ነገሩ አማካኝነት ስለተዛመደና እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በአፀፉ ስለተጠቀሰ ነው፡፡ ሀገር የሚለው ስም፣ ሄዱ በሚለው ግስ ለተጠቀሰው ተግባር መድረሻ ነው፡፡ ልጆቹ ሄደው የሚደርሱበትን ቦታ ያመለክታልና፡፡ እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው ሀረግ የሚዋቀረው፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ወደ ለሚለው መስተዋድድ መሙሊያ በመሆን ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ፣ በዕፀ መዋቅሩ ላይ ክፍት (-) የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ይዘት ወደ ሀገር የሚል ነው፡፡ ይህም የሚታወቀው /-በት/ ከሚለው ድርብ አፀፉ ነው፡፡ አፀፋው የሚያጣቅሰው ይህንኑ ሀረግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በሀረጉ ውስጥ ባለው መስተዋድድና በአፀፋው መስተዋድድ መካከል የቅርፅ ልዩነት አለ፡፡ በሀረጉ ውስጥ መስተዋድዱ ወደ የሚለው ሲሆን፣ በአፀፋው ላይ የሚታየው /-በ/ ሆኖ ነው፡፡

ሁኔታው በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ለምሳሌ፣ ሀገር የሚለው መሪ ስም መድረሻ ሳይሆን፣ መነሻ ወይም መኖሪያ ቢሆን፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ

የሚጠቀሰው በተለየ ሳይሆን፣ በዚሁ /በ/ በሚለው አፀፋ ብቻ ነው፡፡ ልጆቹ <u>የመጡበት</u>፣ <u>የደረሱበት</u>፣ <u>የሚኖሩበት</u>፣ ወዘተ፣ ሀገር፤ ወይም ልጆቹ <u>የበሉበት</u> መሶብ፣ <u>የጠጡበት</u> ዋንጫ፣ ወዘተ፣ ብንል፣ የየሀረጉ መስተዋድድ ቅርፅ ይለያያል እንጅ፣ አፀፋው አይለወጥም፡፡ አፀፋው የተለየ የሚሆነው መስተዋድዳዊ ሀረጉ ለአንድ ድርጊት ተጠቃሚ መሆንን የሚያሳይ ሲሆን ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

አስቴር ለካሳ ገንዘብ ላከችለት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ለካሳ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በግሱ የተገለፀው ድርጊት ፈፃሚ ሳይሆን፣ ተጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህም በግሱ ላይ መስተዋድዳዊው ሀረግ /-ለት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ይህንኑ አረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ብንለውጠው፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ የሚጠቆመው በዚሁ /-ለት/ በሚለው አፀፋ ይሆናል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

[[አስቴር ገንዘብ የላከች-<u>ለት</u>] ሰው] 14

ከላይ በሚታየው አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ የሚታየው፣ <u>ለካሳ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በዚህ ስማዊ ሀረግ ውስጥ አይታይም፡፡ የማይታየውም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ስለሆነና እንደ ማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በግሱ ላይ ብቻ በአፀፋ ስለተጠቀሰ ነው፡፡ አፀፋውም በግልፅ እንደሚታየው፣ /-ለት/ ነው፡፡ ባጭሩ፤ ስለ መስተዋድዳዊ ሀረግ የአፀፋ ስርዓት የሚከተለውን ማለት ይቻላል፡፡ ተጠቃሚነትን ከሚያሳይ መስተዋድዳዊ ሀረግ በስተቀር፣ ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ በተዛማጅነት ሲገባ፣ የሚጠቀሰው /በ/ በሚለው መስተዋድድ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ /-በ/ እና /-ለ/ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች ናቸው፣ /-በ/ ለማንኛውም መስተዋድድ፣ /-ለ/ ተጠቃሚን ለሚያሳይ መስተዋድድ ብቻ፡፡

እስካሁን ድረስ ያየናቸው ተዛማጅ ሀረጎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ የግሱ ተሳቢ ወይም አጎላማሽ የሆኑ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ስማዊ ሀረግ እንዴት እንደሚዛመድ እንመለከታለን፡፡ ለዚህ የሚከተለውን እንይ፡፡

[[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] ልጅ] 15

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣

[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] 16

የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ባለቤቱ አስቴር የሚለው አንስታይ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ስለሆነም በግሱ ላይ /-ች/ በሚለው የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ ምዕላድ ተጠቁሞአል፡፡ የግሱ ተሳቢ ፀጉርዋን የሚለው ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ እሱም እንደዚሁ በግሱ ላይ /-አት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ባለቤትም ሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ በቦታቸው አሉ፣ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ላይ ታዲያ፣ ልጅ ከሚለው መሪ ስም ጋር የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ወይም የግሱ ተሳቢ ሊሆን አይችልም፡፡ እነዚህ በግሀድ ይታያሉና፡፡ ስለዚህም ተዛማጁ ሀረግ ከነዚህ ውጭ የሆነና በአፀፋም የተጠቆመ መሆን አለበት፡፡ ከባለቤትና ከተሳቢ አፀፋ ሌላ፣ በግሱ ላይ የሚታይ ምንም አፀፋ የለም፡፡ በተሳቢው ስማዊ ሀረግ መድረሻ ላይ ግን [-ዋ] </-ኡ-አ/ የምትል ድርብ አፀፋ አለች፡፡ ይህች አፀፋ የምትጠቁመው *ገንዛቢ* (ባለገንዘብ) ስማዊ ሀረግን ነው፡፡ የዚህ አይነት ስማዊ ሀረግ በተሳቢው ስማዊ ሀረግ ውስጥ በድብቅ አለ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አረፍተ ነገሩ ሲተረጎም፣

አስቴር ልጅትዋን ፀጉርዋን ሰራቻት 17

የሚል ይሆናል፡፡


የተዛመደውም ይህ ልጅትዋን የሚለው ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ከዚህ ሀረግ ጋር የተገናዘበው ደግሞ ፀጉር የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሪ ሲሆን፣ ሁለቱን ስሞች፣ ማለትም አስቴር እና ፀጉር የሚሊትን፣ የሚያገናዝበው (የሚያገናኘው) ምዕላድ /-ዋ/ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ልጅትዋን የሚለውን ስም ገንዛቢ፣ ፀጉርዋን የሚለውን ተገናዛቢ፣ እንዲሁም /-ዋ/ን አገናዛቢ የባለቤት አፀፋ ወይም ዘርፍ እንላታለን፡፡ አገናዛቢዋ ምዕላድ የገንዛቢው ሀረግ አፀፋ ነች፡፡ የምትታየውም በተገናዛቢው ስም መድረሻ ላይ ነው፡፡ የባለቤት አፀፋ በመሪ ግስ ላይ እንደሚታይ ሁሉ፣ የገንዛቢ አፀፋም በመሪ ስም ላይ ይታያል፣ ማለት ነው፡፡ ሲጠቃለል፣ አፀፋዎች የሚታዩት በመሪ ላይ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በሚታየው ምሳሌ ውስጥ፣ የተዛመደው ስማዊ ሀረግ ልጅትዋ የሚለው ገንዛቢ ስም ነው፡፡ ይህ ውነት ለመሆኑ ማስረጃው /-ዋ/ በሚለው ምዕላድ መጠቀሱና በግሀድ አለመታየቱ ነው፡፡ በአዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ አለመታየትና በአፀፋ መጠቀስ የተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ምልክት ነው፣ ብለናልና፡፡ ከዚህ አንፃር፣

[[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-አት] ልጅ] 18

የሚለው ስማዊ ሀረግ ውስጣዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

19




ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ መሪ ፀጉርዋን የሚለው ተገናዛቢ ስም ነው፡፡ የዚህ ስም ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ደግሞ (ስሀᵢ)ነው፡፡ የተዛመደውም እሱው ነው፡፡ ስለተዛመደም ፀጉርዋን በሚለው መሪ ስም ላይ በአፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ከአፀፋው ሶስተኛ መደብ፣ እንስታይ ፆታ፣ ነጠላ ቁጥርና ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል፡፡

እስካሁን በዚህ ክፍል ውስጥ ያየነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን፡፡ ለማየት የተነሳነው ውስብስብ ስማዊ ሀረጎችን ነው፡፡ ሀረጎቹ ውስብስብ የሆኑበት ምክንያት አረፍተ ነገራዊ ከሆኑ መሙሊያዎች ወይም ገላጮች ጋር ስለሚዋቀሩ ነው፡፡ መሙሊያዎቹ ስማዊ አረፍተ ነገሮች ሲሆኑ፣ ገሳጮቹ አዛምጅ ግሳዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ የመሪው ስም መሙሊያ ወይም ገላጭ ሆነው በጥገኝነት መግባታቸውን የሚያመለክት /የ/ የሚል ምዕላድ አላቸው፡፡ ይህም ሞይ ያልነው አሀድ ነው፡፡ መዋቅራዊ ዝምድናው ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሲሆን፣ አገባቡም አረፍተ ነገሩን ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡


የስማዊ መሙሊያ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ሲከሰት ወይም ላይከሰት ይችላል፡፡ የሚከሰተው፣ አንድም በመሪው ስም ላይ አፀፋው ሲታይ፣ አለያም /የ/ የምትለዋን ምዕላድ ሲያስቀድም ብቻ ነው፡፡

አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤቱን፣ ወይም ተሳቢውን ወይም መስተዋድዳዊ ሀረጉን ከሚያጎሳምስው ስም ጋር ያዛምዳል፡፡ የሚዛመደው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ በአፀፋ ግን እንደተለመደው ይጠቀሳል፡፡ አፀፋው የሚታየው በግሱ ላይ ነው፡፡ ከአፀፋው አይነት በግሀድ የማይታየውን ተዛማጅ ስም ይዘት ማወቅ ይቻላል፡፡ ባለቤት ወይም ተሳቢ በሆነ ስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ገንዛቢ ስማዊ ሀረግም እንደዚሁ በአፀፋ ሊዛመድ ይችላል፡፡ ሲዛመድም በግሀድ አይከሰትም፡፡ እንደ ማንኛውም ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ አፀፋው በመሪው ላይ ስለሚታይ ይዘቱ ከዚያው ይታወቃል፡፡

ውስብስብ ስማዊ ሀረግ በባለቤትነት ወይም በተሳቢነት ወይም በገላጭነት ሊገባ ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለ ውስብስብ ሀረግን የያዘ አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ውስብስብ ይባላል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

20 (ሀ) [[የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] [ከሸፈ] ]
(ለ) [እኔ [[የአስቴርን ቤት የመስራት አላማ] እደግፋለሁ] ]

የመጀመሪያው ምሳሌ [የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ባለቤት የሆነበትና <u>ከሸፈ</u> ከሚለው ግስ ጋር ውስብስብ አረፍተ ነገር ያዋቀረበት ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ይኸው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ <u>እደግፋለሁ</u> ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ፣ ብሎም ተሳቢ ሆኖ የገባበት ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉት በውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ምክንያት ውስብስብ የሆኑ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ውስጣዊ ቅንጅታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡




ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችንና በነሱ ምክንያት ውስብስብ የሚሆኑ አረፍተ ነገሮችን የአወቃቀር ስርዓት እንመለከታለን።

## ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ክፍል ስለ ግሳዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ አንድ ግስ ከተራ ሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽ እና መስተዓምር ጋር እየተዋቀረ ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ይችላል። ከዚህ አይነት ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ ነው። ይህ ግን የሁሉም ግሶች ባህሪ አይደለም። አንዳንድ ግሶች ከተራ ሳይሆን፣ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ሊዋቀሩ ይችላሉ[4]። በዚህም መሰረት ግሶች

[4] ስለ መሙሊያ አረፍተ ነገሮች ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ።


ይለያያሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚፈጠረው መዋቅር ውስብስብ ወይም ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[[ካሳ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች] [አውቆአል]] 1

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣

[አስቴር ወደ ጎንደር እንደ ሄደች] 2

የሚለው መዋቅር አረፍተ ነገራዊ ነው፡፡ አገባቡም <u>አውቆአል</u> ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ነው፡፡ ግሱ ከዚሁ አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ሲቀናጅ የሚፈጥረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ እወቃቀር የሚከተለውን ይመስላል፡፡




3

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች የሚለው አረፍተ ነገር አውቆአል ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ገብቶአል፡፡ መሙሊያው አረፍተ ነገር እንደ የሚለው መስተዋድድና አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች የሚለው አረፍተ ነገር ቅንጅት ነው፡፡ መስተዋድዱ፣ አረፍተ ነገሩ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ፣ የግሱ መሙሊያ ሆኖ በጥገኝነት የገባ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ቀደም ሲል ስለ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ በመሙሊያነት ወይም በአጎላማሽነት የሚገባ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ምዕላድ እንደሚታወቅ ገልፀን ነበር፡፡ አሁንም በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምናየው ሁኔታ ይኸው ነው፡፡ እንደ የሚለው መስተዋድድ፣

አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች 4

የሚለው አረፍተ ነገር በሞይነት መግባቱን ያመለክታል፡፡ አገባቡም እንደ ማንኛውም የዚህ አይነት ምዕላድ፣ አረፍተ ነገሩን ተከትሎ ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ጥገኝነትን የሚያመለክቱ ምዕላዶች ሞይ እንደሚባሉ፣ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር ይባሉ እንደነበርም በክፍል ሁለት ስለ ቃላት ክፍል ስንወያይ ጠቅሰናል፡፡ መስተፃምር የሚያሰኛቸው ከአረፍተ ነገር ጋር መግባታቸው ብቻ ነው፡፡ በሌላው ባህሪያቸው ከመስተዋድድ እንደማይለዩ ገልፀናል፡፡

በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ጥገኛ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ሞይ ሲታወቅ፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ተመሳሳይ አረፍተ ነገር ግን እንደ በሚል መስተዋድዳዊ ሞይ ይለያል፡፡ ሁኔታው ግን በዚህ ብቻ አያቆምም፡፡ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ አንዳንድ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችም /የ/ በሚለው ሞይ ሊታወቁ ይችላሉ፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡


[[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] ይመስላል] 5

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] 6

የሚለው ጥገኛ አረፍተ ነገር ይመስላል የሚለው ግስ መሙሊያ ነው፡፡ ስለሆነም በግሱ ላይ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ አስቀድሞአል፡፡ ይህችም ሞይ ምዕላድ ስትሆን፣ ታህታይ ቦታዋ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ነው፡፡ ይህንንም ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

7




የአረፍተ ነገሩን ውስጣዊ ቅንጅት ከፍ ብለን ያየነው ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ አንደግመውም፡፡ ከእሱ ይልቅ <u>ይመስላል</u> ስለሚለው ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ጥቂት ገለፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ግስ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ንዑስ ግሳዊ ሀረትን ይመሰርታል፡፡ እንደዚሁም ከገላጭ አረፍተ ነገር ጋር ሆኖ እቢይ ግሳዊ ሀረትን ይመሰርታል፡፡ ይሁን እንጅ ባለቤት የለውም፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ የባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (-) ይሆናል፡፡ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግን ቦታው አንድም ክፍት እንደሆነ ይቀራል፣ አለያም በመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ይሸፈናል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) [—[ልጆቹ [ስራ የሚሰሩ] ] ይመስላል] 8
(ለ) [ልጆቹ [---[ስራ የሚሰሩ] ] ይመስላሉ]

በምሳሌ (ሀ) [ስራ የሚሰሩ] የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ይህን <u>የሚሰሩ</u> ከሚለው ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው የብዙ ቁጥር አፀፋ ማወቅ ይቻላል፡፡ <u>ይመስላል</u> የሚለው የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ፣ የባለቤት ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው፡፡ ከግሱ መነሻ ላይ /ይ-/ የሚል ምዕላድ ይታያል፡፡ ይህም ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነን ባለቤት ይጠቁማል፡፡ ይህም <u>የአቃፊው</u> አረፍተ ነገር ባለቤት መሆን አለበት፡፡ የ<u>ታቃፊው</u> አረፍተ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው የብዙ ቁጥር ስም ነው፡

ብለናልና፡፡ ሁለተኛም ይመስላል የሚለው ግስ ባለቤት እንደሌለው ከፍ ሲል ገልፀናል፡፡

ይህ እውነት ከሆነ፣ /ይ-/ በሚለው ምዕላድ የሚጠቀሰው የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ አንድ ግስ በታህታይ መዋቅር ባለቤት የለውም ሲባል፣ ድርጊት ፈፃሚ ወይም ሁዋኝ ባለቤት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር፣ የእንደዚህ አይነት ግስ የባለቤት ቦታ ክፍት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፡ ማንኛውም አረፍተ ነገር በላዕላይ መዋቅር የግድ ባለቤት ማግኘት አለበት፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም አረፍተ ነገር በይዘቱ ብቻ ሳይሆን፣ በቅርፁም የተሙዋላ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ባለቤት የሌለው አረፍተ ነገር ሙሉ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ሙሉ እንዲሆን ከፈለግን፣ አድራጊም ሆነ ሁዋኝ ያልሆነ፣ ግን በባለቤት ቦታ ሊገኝ የሚችል፣ የይስሙላ ባለቤት (ለስም ብቻ የገባ) በላዕላይ መዋቅር ማስገባት አለብን፡፡ ይህም የይስሙላ ባለቤት በሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አፀፋ፣ ማለትም በ/ይ-/ ብቻ ይጠቀሳል፡፡ በግሀድ ግን አይወጣም፡፡ ቋንቋዋው የዚህ አይነት ግሀድ ባለቤት የለውምና፡፡

እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቋንቋዎች፣ እንደዚህ ያለ የይስሙላ ባለቤት የሚሆን ተውላጠ ስም አለ፡፡ እሱም it ወይም there ነው፡፡ ይህ ተውላጠ ስም ደግሞ በአፀፋ አይጠቀስም፣ ምክንያቱም ቋንቋዋው የአፀፋ ምዕላድ የለውም፡፡ በሀገራችን ቋንቋዎች ደግሞ እንደነዚህ ያሉ የይስሙላ ባለቤቶች፣ እንደ it ወይም there በነፃ ተውላጠ ስም መልክ አይከሰቱም፡፡ የሚከሰቱት /ይ-/ በሚለው አፀፋ ምዕላድ ብቻ ነው፡፡ በአጭሩ፣ እንደ አማርኛ ባሉ የሀገራችን ቋንቋዎች it እና there መደበኛ ተውላጠ ስማዊ ቅርፅ የላቸውም፡፡ እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቋንቋዎች ደግሞ፣ መደበኛ ቅርፅ አላቸው፣ በአፀፋ ግን አይጠቀሱም፡፡

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ይመስላል የነበረው ግስ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ ይመስላሉ የሚል ሆኖአል፡፡ የብዙ ቁጥር፣ የባለቤት ስማዊ ሀረግ አፀፋ የሆነውን /-አ/ን ያሳያል ማለት ነው፡፡ ይህም የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ልጆቹ የሚለው የብዙ ቁጥር ስማዊ ሀረግ መሆኑን ያሳያል፡፡ የሚሰሩ በሚለው ግስ መድረሻ ላይም ሀረጉ በዚሁ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ስለዚህም ባለቤትነቱ ለእቃፊውም ለዕቅፉም አረፍተ ነገር ነው፡፡ ለእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ለመሆን፣ በምሳሌ (ሀ) ከሚታይበት ታህታይ ቦታው ተነስቶ፣ ከፍት ወደሆነው ወደ እቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ መሄድ አለበት፡፡ በዚያ ሆኖ የእቃፊውም ሆነ የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ሊሆን ይችላል[5]፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው እንደ ይመስላል ያሉ ግሶች በመሰረቱ በባህሪያቸው ባለቤት-የለሽ በመሆናቸው ነው፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት፡፡

---

[5] ስለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ሁኔታ ባየ (1988፣ 1994)ን ይመልከቱ፡፡

(ሀ) [---[ልጆቹ ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል]] 9
(ለ) [ልጆቹ [---ስራ እንዲሰሩ ይደረጋሉ]]

ይደረጋል የሚለው ግስ ተገብሮአዊ ነው፡፡ ታህታይ ቅርፁ /ይ-ት-ደረጋል/ ነው፡፡ የተገብሮ ግሶች፣ ይመስላል እንደሚለው ግስ፣ ባለቤት-የለሽ ናቸው፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ የባለቤታቸው ቦታ ሁል ጊዜ ክፍት ነው፡፡ በላዕላይ መዋቅር ግን አረፍተ ነገሮች በቅርፃቸው ተሙዋልተው መገኘት ስላለባቸው፣ የግድ ባለቤት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህም it የሚለው የይስሙላ ባለቤት ይገባላቸዋል፡፡ ይህም ተውላጠ ስም /ይ-/ በሚለው አፀፋ ብቻ በግሱ መነሻ ላይ ይከሰታል፡፡ ይህ ሲሆን የአረፍተ ነገሩ ቅርፅ 9(ሀ)ን ይመስላል፡፡

በሌላ በኩል፣ ልጆቹ የሚለው የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት፣ ከቦታው ወጥቶ በአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ ሊገባና የአቃፊውም ሆነ የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ይደረጋል የነበረው ግስ የብዙ ቁጥር ቅርፅ ይይዝና ይደረጋሉ ይሆናል፡፡ ወደተነሳንበት የውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ጉዳይ እንመለስ፡፡

ማንኛውም ሳቢ ግስ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር እየተዋቀረ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)፣ የተለያየ ተውሳከ ግሳዊ ተግባር ካላቸው አረፍተ ነገሮች ጋር እየተቀናጀ፣ አቢይ ሀረጉን ይመሰርታል፡፡ በክፍል ሁለት ስለ ተውሳከ ግስ ስንወያይ፣ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት በመስተዋድዳዊ ሀረጎችና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች እንደሚገለፁ፣ ለዚህም ምክንያቱ ቁዋንቁዋው በቂ መደበኛ ተውሳከ ግስ ስለሌለው እንደሆነ ገልፀን ነበር፡፡ በዚያ መሰረት ከንዑስ ግሳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩና ተውሳከ ግሳዊ ተግባር የሚያሳዩ ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ባህሪ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) [ካሳ [[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት እንደሄደች] [ምሳውን በላ]]] 10


(ለ) [ካሳ [[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት ስለሄደች] [ተደሰተ]]]

በመጀመሪያው ምሳሌ በላ የሚለው ግስ ሳቢ ነው፡፡ ስለሆነም ምሳውን ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ምሳውን በላ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ ከዚህ ሀረግ በፊት የሚገኘው፣ ማለትም፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት እንደሄደች] 11

የሚለው ክፍል፣ ገላጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ገላጭነቱም [ምሳውን በላ] ለሚለው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ ምሳ የመብላቱ ድርጊት መቸ እንደተፈፀመ ይገልፃል፡፡ ከዚህ ተግባሩ በመነሳት መዋቅሩን አረፍተ ነገራዊ የጊዜ ተውሳከ ግስ ልንለው

እንችላለን፡፡ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ እንዴት እንደሚመሰርት በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡





በግልፅ እንደሚታየው፣ ገላጩ አረፍተ ነገር (እነ') ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) መሰርቶአል፡፡ የአረፍተ ነገሩ አወራረድም ከዚሁ ሀረግ እንጉዋ ላይ ነው፡፡ ይህ የማንኛውም ገላጭ መዋቅር ባህሪ እንደሆነ በክፍል ሁለት ስለ ሀረግ ስንወያይ ተገንዝበናል፡፡ የአረፍተ ነገሩ ሞይ እንደ የሚለው ምዕላድ ሲሆን፣ እሱም እንደማንኛውም ሞይ አረፍተ ነገሩን ተከትሉ በስተቀኝ በኩል ገብቶአል፡፡

በሁለተኛው ምሳሌ (10ለ) ውስጥ ያለው መዋቅራዊ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ተደሰተ የሚለው ግስ ኢሳቢ ነው፡፡ ስለዚህም ተሳቢ የለውም፡፡ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርተው ብቻውን በመቆም ነው፡፡ ይህን ንዑስ ሀረግ የሚገልፀው፣

[እስቴር ወደ ትምህርት ቤት ስለሄደች] 13

የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የሚገልፀውም የደስታውን ምክንያት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር የምክንያት ተውሳከ ግስ ይባላል፡፡ ከንዑስ ሀረግ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነት እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡

14




እስካሁን ድረስ ያየናቸው መሙሊያና አጎላማሽ (ገላጭ) አረፍተ ነገሮች፣ ግሳዊ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ግሳዊ አረፍተ ነገሮች የሚባሉት፣ ግሳዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። የነሱ አቻ የሆኑ መሙሊያና ገላጭ ስማዊ አረፍተ ነገሮችም አሉ። እነዚህ በግሳዊ ሀረግ ፋንታ፣ ስማዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው። አንዳንዶቹን ስለ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ስንወያይ አይተናቸዋል። ከዚህ ቀጥለን እንደነዚህ ያሉ ስማዊ አረፍተ ነገሮችን በመሙሊያነትና በገላጭነት የሚያስገቡ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችን ባህሪ እንመረምራለን። ከዚያ በፊት ግን ስማዊ አረፍተ ነገሮች ውሱንና ኢውሱን ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ እናስገነዝባለን። ውሱን የሚባሉት የባለቤት አፀፋ ያላቸው ሲሆኑ፣ ኢውሱን የሚባሉት አፀፋ የሌላቸው ናቸው። በውስኖቹ ላይ የሚታየው የባለቤት አፀፋ ዘርፍ ነው። በመሆኑም በግሱ ላይ ከሚታየው የባለቤት አፀፋ በቅርፁ ይለያል። ጉዳዩታውን በርባታው ክፍል ያየነው ቢሆንም፣ ለማስታወስ ያህል አፀፋዎቹን ከዚህ በታች እንደገና እንዘረዝራቸዋለን።

15

| | ግሳዊ | ስማዊ |
|---|---|---|
| 1 | ሰበር-ሁ | መስበር-ኤ[6] |
| 2 | ሰበር-ህ | መስበር-ህ |
| እን | ሰበር-ሽ | መስበር-ሽ |
| 3 | ሰበር-ኧ | መስበር-ኡ |
| እን | ሰበር-ኧች | መስበር-ዋ |
| ብዙ | ሰበር-ን | መስበር-ኣችን |
| | ሰበር-ኣችሁ | መስበር-ኣችሁ |
| | ሰበር-ኡ | መስበር-ኣቸው |

[6] የአፀፋዎችን ባህሪና መዋቅራዊ ተግባር በተመለከተ ባየ(1988፣ 1994፣ 2001፣ 2004)ን እንዲሁም ግርማ (1994)ን ይመልከቱ።

ግሶቹ ያላፀፋዎቹ በአረፍተ ነገር ውስጥ ሊገቡ አይችሉም። ባለቤቱን የሚጠቁሙት አፀፋዎች በግሱ ላይ የግድ መገኘት አለባቸው። በተጨማሪም ግሶቹ የተሳቢ አፀፋንና ጊዜን ሊያሳዩ ይችላሉ። ስሞቹ ግን ያለምንም አፀፋ ሊገኙ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ባለቤቱ /የ/ በሚል ምዕላድ ሊለይ ስለሚችል ነው። ከዚህ የተነሳ ነው፣ እንደ መስበር ባሉ ስሞች አማካኝነት የሚመሰረቱ አረፍተ ነገሮች ውሱንና ኢውሱን ተብለው በሁለት የሚከፈሉት።

በአፀፋ የተጠቀሰ ሀረግ በግሀድ ሊከሰት ወይም ላይከሰት ይችላል። በግሀድ የሚከሰተው አንድም በአፀፋ ሲጠቀስ አለያም /የ/ በምትለዋ ምዕላድ ሊደገፍ ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [[አስቴር ወደ ጎንደር መሄድ-ዋ-ን] ሰምቶአል] 16
(ለ) ካሳ [[የአስቴርን ወደ ጎንደር መሄድ] ሰምቶአል]
(ሐ) ካሳ [[----- ወደ ጎንደር ለመሄድ] ይፈልጋል]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ሰምቶአል የሚለው ሳቢ ግስ፣

[አስቴር ወደ ጎንደር መሄድ-ዋ-ን] 17

የሚለውን ስማዊ አረፍተ ነገር በመሙሊያነት ይዞ፣ ወደ ጎንደር መሄድዋን ሰምቶአል የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል። መሙሊያው አረፍተ ነገር የተዋቀረው ወደ ጎንደር መሄድዋን ከሚለው ስማዊ ሀረግና አስቴር ከሚለው ባለቤት ነው። ወደ ጎንደር መሄድዋን የሚለው ሀረግ መሪ የባለቤት አፀፋ ስለሚያሳይ፣ መሙሊያው አረፍተ ነገር ውሱን ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ውሱን የሆነ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ሊከሰት ይችላል። ባይከሰትም ይዘቱ ከመሪው ላይ ከሚታየው አፀፋ ሊታወቅ ይችላል።


በምሳሌ (ለ) ውስጥ የሚታየው መሙሊያ አረፍተ ነገር ኢውሱን ነው። ምክንያቱም መሄድ የሚለው መሪ ስም የባለቤት አፀፋ አልያዘም። ስለዚህም አስቴር የሚለው ባለቤት ስም በግሀድ ሊከሰት የሚችለው /የ/ የምትለዋን ምዕላድ ሲያሳይ ብቻ ነው። በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የምትታየው /-ን/ የምትለዋ ምዕላድ አረፍተ ነገሩ ተሳቢ ሆኖ መግባቱን የምታመለክት የተሳቢ ምልክት ነች። አገባብዋ ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው፣ ከባለቤቱ አፀፋ፣ ወይም /የ/ን አስቀድሞ፣ በግሀድ ከሚታየው ባለቤት ስም ቀጥሎ ነው።

በምሳሌ (ሐ) መሄድ የሚለው ስም የባለቤት አፀፋ የለውም። ስለዚህም ባለቤቱ በግሀድ ሊከሰት አልቻለም። ቦታው ግን በሰረዝ (---) የተመለከተው ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ እንዳየነው፣ ባለቤቱ /የ/ን አስቀድሞ በግሀድ ሊከሰት ይችላል። ይህ ሲሆን፣ ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል።

* [ካሳ [የካሳ ወደ ጎንደር (ለ)መሄድ] ይፈልጋል] 18

ከስዋሰው ህግጋት አንፃር ሲታይ፣ ይህ መዋቅር ተቀባይነት አለው፡፡ ከትርጉም አንፃር ግን ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤትና ይፈልጋል በሚለው ግሰ የሚመራው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት የሚጠቁሙት አንድን ሰው በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ከመከሰት ይታቀባል፡፡ ማንነቱ ከእናቱ (ከአቃፊው) አረፍተ ነገር ባለቤት ይዘት ይታወቃል፡፡

[ወደ ጎንደር ለመሄድ] በሚለው ውስጥ የምትታየው /ለ/ መስተዋድዳዊ ሞይ ነች፡፡ አገባብዋም እንደማንኛውም ሞይ መሙሊያውን አረፍተ ነገር ተከትላ ነው፡፡ የሁሉንም ስማዊ አረፍተ ነገሮችና የግሱን መዋቅራዊ ግንኙነት አጠቃለን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡




19

ይህ የኢውሱኑ መሙሊያ አረፍተ ነገርና፣ <u>ይፈልጋል</u> የሚለው ሳቢ ግስ መዋቅራዊ ግንኙነት ነው። የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አይታይም። ቦታው በሰረዝ የተመለከተው ነው። <u>መሄድ</u> የሚለው መሪ ስም የባለቤት አፀፋ በሚያሳይበት ጊዜ፣ ባለቤቱ በሰረዝ በተመለከተው ቦታው ላይ በግሀድ ሊከሰት ይችላል። በዚህን ጊዜ ሞዬ አይታይም። የሚታየው የተሳቢ ምልክት የሆነው /-ን/ የሚለው ምዕላድ ነው። ይህ ምዕላድ ውሱን ከሆኑ ተሳቢ ሀረጎች ጋር ቁርኝት ስላለው፣ እሱ ይከሰትና ሞዬ ከቦታው ይጠፋል[7]። ይህም የሚሆነው በላዕላይ መዋቅር ነው። ቁዋንቁዋው ሁለቱ ምዕላዶች በላዕላይ መዋቅር ተከታትለው እንዲመጡ የሚፈቅድ አይመስልም[8]።

ከሰማዊም ይሁን ከግሳዊ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችና ከግስ የሚመሰረቱ ንዑስ ሀረጎች ከተለያዩ አጎላማሽ አረፍተ ነገሮች ጋር በመዋቀር አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርቱ ይችላሉ። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

]አስቴር [[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] [[ካሳ መምጣቱን] ሰማች]]] 20

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ <u>ሰማች</u> የሚለው ሳቢ ግስ፣ [ካሳ መምጣቱን] ከሚለው ሰማዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣ [ካሳ መምጣቱን ሰማች] የሚለውን ንሁስ ግሳዊ ሀረግ መሰርቶአል። መሙሊያው ሰማዊ አረፍተ ነገር አፀፋ ስላለው ውሱን ነው። ስለዚህም ባለቤቱ ካሳ በግሀድ ሊከሰት ችሎአል። ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ በተራው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] 21

ከሚለው ግሳዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣

---

7 ከዚህ ላይ /-ን/ የተሳቢ ምዕላድ ሳይሆን፣ ሞይ መስተዋድድ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል። /-ን/ በመስተዋድድነት ሲገባ ቀደም ብለን አይተናል። እንደ ከሚለው ሞይ ጋር ተከታትሎ የማይመጣውም ለዚሁ ነው። የአንድን አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆን ለማሳየት ሁለት ሞይ አያስፈልግም።

8 ይህ ገደብ በሌሎች ምዕላዶችም ይታያል። ለምሳሌ /የ/ የሚለው አገናዛቢ ምዕላድ ከማንኛውም መስተዋድድ በሁዋላ ሲገባ፣ በግሀድ አይታይም። ስለዚህም ለምሳሌ፣ የ-<u>ካሳ</u> ልጅ የሚለው አገናዛቢ ሰማዊ ሀረግ፣ ]ለካሳ ልጅ]፣ [ወደ ካሳ ልጅ]፣ [እንደ ካሳ ልጅ]፣ ወዘተ፣ ይሆናል። በዚህ ምክንያት ቀደምት ሊቃውንት ው<u>ስጡ-የ</u> እና ግልፀ-የ የሚል አጠራር ነበራቸው። የ<u>ካሳ</u> ልጅ በሚለው መነሻ ላይ የሚታየው /የ/ <u>ግል</u>ፀ-የ ሲሆን፣ ከየመስተዋድዱ ቀጥሎ የሚመጣውና በግሀድ የማይታየው /የ-/ <u>ውስጡ-የ</u> ነው።

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደ ሄዱ ካሳ መምጣቱን ሰማች] 22

የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] የሚለው ገሳጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የሚገልፀው ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ አገላለፁም ካሳ የመጣበትን ጊዜ በመጥቀስ ነው፡፡ ስለዚህም አረፍተ ነገራዊ የጊዜ ተውሳከ ግስ ልንለው እንችላለን፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አረፍተ ነገሩ ግሳዊ ነው፡፡ ስማዊ አቻው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው] 23

የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ አገባቡ አሁንም በገሳጭነት ነው፡፡ ሲገባም ከላይ በተራ ቁጥር (20) የተገለፀው ምሳሌ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው ካሳ መምጣቱን ሰማች] 24


በግልፅ እንደሚታየው፣ መሙሊያውም ሆነ ገሳጩ አረፍተ ነገር ስማዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፡ ሁለቱም ግሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን፣ መዋቅሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

(ሀ) [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች] 25
(ለ) ?[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች]

የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ትንሽ አጠራጣሪ ሊመስል ይችላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የገሳጩና የመሙሊያው አረፍተ ነገር ሞዪ አንድ አይነት ቃል መሆኑ ነው፡፡ ከትርጉም አኳያ ሲታዩ፣ ልጆቹ እንደሄዱ እና ካሳ እንደመጣ ሰማች የሚሉት መዋቅሮች ሁለት ተከታታይ ድርጊቶችን ያመለክታሉ። ከምሳሌዎቹ ማንኛውም አይነት አረፍተ ነገር በመሙሊያነትም ሆነ በገሳጭነት ሊገባ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ በአጠቃቀም ደረጃ፣ ገሳጩ መዋቅር ግሳዊ ሆኖ መሙሊያው ስማዊ ቢሆን፣ አረፍተ ነገሩ የበለጠ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

የንዑስ ሀረጉን አወቃቀር በምሳሌ (22) አማካኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

26





እንደዚህ ያሉ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎች ቀደም ሲል እንዳየናቸው ካሉ ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ጋር ሲዋቀሩ በጣም ውስብስብ የሆነ አረፍተ ነገር ይፈጥራሉ፡፡ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[[አስቴርን የሰደበቻት ሴት] [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ [ካሳ መምጣቱን ሰማች]]] 27

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት [አስቴርን የሰደበቻት ሴት] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጉ [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ መምጣቱን

ሰማች] የሚለው ክፍል ነው፡፡ የሁለቱን አወቃቀር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡ የግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (26) በዝርዝር የሚታይ ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ በጥቅሉ ብቻ እናቀርበዋለን፡፡ ስማዊ ሀረጉን በዝርዝር እንመለከተዋለን፡፡

28



በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሶስት ጥገኛ አረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም በባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ሰደበቻት በሚለው ግስ የሚመራው ገላጭ፣ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ፣ ሄዱ በሚለው ግስ የሚመራ ገላጭና፣ መምጣቷን በሚለው ስም የሚመራው መሙሊያ አረፍተ ነገር ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሩ ከዚህም የበለጠ ሊውስበለብ ይችላል፡፡ ይህን ባደረገ ቁጥር እየረዘመ ስለሚሄድ፣ ለማስታወስ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም የእያንዳንዱ አረፍተ ነገር የውስብስብነት ደረጃ በተጠቃሚው የማስታዎስ ችሎታ ይወሰናል፡፡ ከስርዓት አንፃር ሲታይ ግን የማንኛውም አረፍተ ነገር መጠን ገደብ የለውም፡፡ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> ትናንት በግ የሸጠው ነጋዴ ያመጣውን የሰንጼ ዳቦ የሰረቀውን ልጅ የገረፈችው ሴት አለቴር የምትሸጠውን የገብስ ጠላ ጠጥቶ አልከፍልም በማለት እየዛተ የሄደውን ረዥም ልጅ የሰደበችው ነች፡፡ 29

ይህ ከ(12) ግላዊና ከአንድ ስማዊ ሀረግ በየደረጃው የተዋቀረ አንድ ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ከዚህም የበለጠ ሊረዝም ይችላል፡፡ ቢረዝምም መጠኑ ከአንድ አረፍተ ነገር አያልፍም፡፡ የሀረጎቹ መሪዎች የተሰመረባቸው ቃላት ናቸው፡፡ ዋናው አረፍተ ነገር ነች በሚለው ግስ መሪነት ከተመሰረተው ግሳዊ ሀረግና ሴት በሚለው ስም መሪነት ከተዋቀረው ስማዊ ሀረግ የተቀናጀ ነው፡፡ በተራ መልኩ ሲቀመጥ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[[.... ሴት] [.... ነች]] 30

ይህ እናት ወይም አቃፊ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ በሌሎቹ በተሰመረባቸው ቃላት መሪነት በተመሰረቱት ሀረጎች አማካኝነት የተዋቀሩት አረፍተ ነገሮች በሙሉ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ አንዱ አረፍተ ነገር በሌላው አረፍተ ነገር ሀረግ ውስጥ እየገባ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ የሚሆንበት ስርዓት ነው፡፡ ይህን በዚህ እንተወውና ወደሌላ ጉዳይ እንሂድ፡፡ ከዚያ በፊት ግን በተራ ቁጥር (29) የተመከተውን አረፍተ ነገር ትንተና እንዲሞክሩት እንጋብዛለን፡፡

እስካሁን ያየናቸው ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎች በቃላዊ ግስ መሪነት የሚዋቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በምዕላድ መሪነት የሚዋቀሩ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችን ውስጣዊ ቅንጅት እንመለከታለን፡፡ ጉዳዩ በክፍል ሁለት፣ ስለ ቃላት ምስረታ ስንወያይ ካየነው ከአድራጊና ከአስደራጊ አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ያኔ አድራጊና አስደራጊ ምዕላዶች አንድ ግስ በሚፈልገው የመሙሊያ ሀረግ መጠን ላይ አስተዋፅዖ እንዳላቸው ገልፀን ነበር፡፡ ከዚያ አኳር፣ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡፡

(ሀ) ቡና ፈሳ 31
(ለ) አሰቴር ቡና አፈሳች
(መ) ካሳ አሰቴርን ቡና አስፈሳት

<u>ፈሳ</u> የሚለው ኢሳቢ የድርጊት (ደራጊ) አምድ ነው፡፡ ኢሳቢ በመሆኑ መሙሊያ የለውም፡፡ ድርጊት ተቀባይ የሆነ ባለቤት ግን አለው፡፡ እሱም <u>ቡና</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ከዚህ ኢሳቢ አምድ መነሻ ላይ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ኢሳቢና ደራጊ የነበረውን አምድ፣ ሳቢና አድራጊ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሳቢ ግስ ደግሞ የግድ መሙሊያ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም አምዱ <u>ቡና</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር በምሳሌ (ለ) እንደሚታየው ሆኖ ይዋቀራል፡፡ <u>አሰቴር</u> የሚለው ስም ለዚሁ አድራጊ ግስ ባለቤት ሆኖ ይገባል፡፡ ከዚሁ ሳቢና አድራጊ አምድ መነሻ ላይ /አስ-/ የሚለው ምዕላድ ሲጨመር፣ አድራጊ የነበረው አምድ አስደራጊ ይሆናል፡፡ አስደራጊ አምድ ሁለት መሙሊያ የግድ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም <u>አሰቴር</u> የሚለውን ሀረግ በሁለተኛ መሙሊያነት ይወስድና በዚህ ስም ፋንታ ባለቤት የሚሆን ሌላ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል፡፡ በዚህም ምክንያት <u>ካሳ</u> የሚለውን ስም በባለቤትነት ይወስድና በምሳሌ (መ) እንደሚታየው ያለ ውስብስብ አረፍተ ነገር ይመሰርታል፡፡ የምሳሌ (መ) ትርጉምም፣

ካሳ አሰቴርን ቡና እንድታፈላ (/ት-አፍኽላ/) አደረገ 32

የሚል ነው፡፡

በዚህ ምሳሌ ውስጥ <u>እንድታፈላ</u> በሚለው ላይ /አስ-/ የሚል ምዕላድ የለም፡፡ በእሱ ፋንታ <u>አደረገ</u> የሚል ነፃ ግስ አለ፡፡ /አስ-/ እና ይህ ግስ አቻ ናቸው፣ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ ምሳሌዎች፣ ማለትም በ31(መ) እና በዚህ ምሳሌ መካከል የትርጉም ልዩነት የለም፡፡ በሌላ አባባል፣ /አስ-/ የሚለው አስር ምዕላድና <u>አደረገ</u> የሚለው መደበኛ ግስ በግብር አንድ ናቸው፡፡ ሁለቱም አስደራጊ ናቸውና፡፡ የሚለያዩት በቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም አንደኛው አሰር ሊሆን፣ ሌላኛው ሙሉ ግስ መሆኑና ከእሱ ጋር የሚዋቀረው አረፍተ ነገርም ሞይ ያለው መሆኑ ነው፡፡


በአንፃሩ <u>ካሳ አሰቴርን ቡና አስፈሳት፣</u> የሚለው ተራ እንጅ ውስብስብ አረፍተ ነገር ላይመስል ይችላል፡፡ ሞይ-አልባ መሆኑም ተራ ሊያሰኘው ይችላል፡፡ ዋናው መለኪያ ግን ሞይ አለሞኖሩ ሳይሆን፣ መዋቅሩን የሚመራው የግስ መጠንና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ መዋቅሩ የአንድ ደራጊና የአንድ አስደራጊ አምድ ቅንጅት ነው፡፡ ርግጥ፣ በላዕላይ መዋቅር ሁለቱ አምዶች አንድ አካል ስለሚሆኑና መዋቅሮቹም ስለሚዋሀዱ ተራ አረፍተ ነገር ሊመስሉ ይችላሉ[9]፡፡

በዚሁ መንፈስ የምሳሌ 31(መ)ን ግሳዊ ሀረግ አቀነባበር በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

---

[9] ርግጥ፣ የቃላዊውን ግስና የምዕላዳዊውን ግስ ግንኙነት በአዕማድ ምስረታው ላይ ማየታችን ግልፅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ምዕላዳዊ ግሶች መዋቅራዊ ቦታቸው ላይ ላይገኙ ይችላሉ፡፡ ለአቀራረብ ግልፅነት ሲባል ግን ከዚህ በታች በሚታየው መዋቅር (33) በቦታቸው ላይ እንዲታዩ ተደርጓል፡፡

33



ከዕፀ-መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ /አስ-/ የሚለው አስደራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው፡፡ [አስቴር...አ-ች] የሚለው አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ነው፡፡ ሞይ የለውም፡ ስለዚህም ሞይ-የለሽ ንዑስ አረፍተ ነገር ልንለው እንችላለን፡፡ ሞይነቱ ለምዕላዳዊው ግስ ለ/አስ-/ ነው፡፡

/አ-/ የሚለው አድራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው፡፡ እሱም [ቡና ፈላ] ከሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግላዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ ይህም አረፍተ ነገር [አስቴር...አ-ች] እንደሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውም፡፡ ፈል- የሚለው ግስ ባለቤት ቡና የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ግሱ /አ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ሲዋሀድ፣ ቡና የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ የዚህ ውሁድ ግስ ተሳቢ ይሆናል፡፡ ውሁዱ ግስ ባለቤት ያስፈልገዋል፡፡ ስለዚህም አስቴር የሚለውን ስማዊ ሀረግ ባለቤት አድርጎ በመውሰድ [አስቴር ቡና አፈላች] የሚለውን አድራጊ አረፍተ ነገር ይመሰርታል፡፡ አፈላ የሚለው ውሁድ ግስ በተራው /አስ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ይዋሀድና /አስ-አ-ፈላ/ ይሆናል፡፡ /አስ-/ እና /አ-/ ተከታትለው ሲገኙ፣ /አ-/ ይገደፋል፡፡ ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግሱ [አስፈላ] የሚል ይሆናል፡፡

አስፈላ የሚለው አስደራጊ ግስ ተሳቢ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ አስቴር የሚለውን ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ እንደ ተሳቢ አድርጎ ይወስድና፣ እንደ ማንኛውም ግስ ባለቤት የሚሆን እንደ ካሳ ያለ ሌላ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል፡፡


አደረገ የሚለው ተራ አድራጊ ግስ ነው፡፡ /አስ-/ በሚለው አስደራጊ ምዕላድ አማካኝነት ድርብ አድራጊ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ቅርፁ አስደረገ የሚል ይሆናል፡፡ የዚህ ድርብ አድራጊ ግስ መዋቅራዊ ይዘት እንደሚከተለው ነው፡፡

ካሳ አስቴርን ቡና እንድታፈላ አስደረጋት 34

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አራት ግሶች አሉ፡፡ እነሱም ፈላ ፣ አ- ፣ አደረገ እና አስ- ናቸው፡፡ ፈላ እና አደረገ መደበኛ ቃላዊ ግሶች ናቸው፡፡ አ- እና አስ- ምዕላዳዊ ግሶች ናቸው፡፡ ከምዕላድም አለር ምዕላድ ናቸው፡፡ በዚህም ቀደም ሲል ስለ ምስረታ ስንወያይ ካየናቸው ከአለር አምዶች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣ ካሳ በአንድ ሌላ ሰው አማካኝነት አስቴር ቡና እንዲፈላ እንድታደርግ አደረገ የሚል ነው፡፡ ከላይ እንደገለፅነው፣ አራት ግሶች ካሉ፣ አራት አረፍተ ነገሮች አሉ፣ ማለት ነው፡፡ እነዚህንም እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

35


አነ
ስሀ
ግሀ
ስ
ግሀ1
ካሳ
አነ'
ግ
አነ
ግ:ይ
አለ-(-አት)
ስሀ
ግሀ
--
ስ
ግሀ1
-
አነ'
ግ
አነ
ሞይ
-ደረግ
ስሀ
ግሀ
እንደ
ስ
አስቴር
አነ'
ግ
አነ
ሞይ
ስሀ
ግሀ
ት-አ-
ስ
ግ
--
ቡና
ፈላ

ይህ በታህታይ መዋቅር የሚታየው አቀነጃጀት ሲሆን፣ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ፣ ፈላ የሚለው አምድ ት-አ- ከሚለው አድራጊ ምዕላድ ጋር ይገናኝና ት-አ-ፈላ ይሆናል፡፡ ይህም እንድ- ከሚለው ሞይ ጋር ተገናኝቶ እንድታፈላ ይሆናል፡፡ በዚህ ግስ መሪነት የተመሰረተው ግሳዊ ሀረግ ባለቤትም አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ -ደረገ በሚለው ደራጊ ግስ መሪነት የተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ በግህድ ያልተጠቀሰውና ቦታው በነጠብጣብ የተመለከተው ነው፡፡ ደረገ የሚለው አስር አምድ አስ- ከሚለው ምዕላድ ጋር ተገናኝቶ አስደረገ ይሆናል፡፡ /አስ-/ የሚለው ምዕላድ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ሲሆን፣ ካሳ ደግሞ የዚሁ አረፍተ ነገር ባለቤት ነው፡፡ ርግጥ፣ እንደ /አስ-/ ያለ ጥገኛ ምዕላድ እንዴት እንደ ግስ ሊቆጠር ይችላል? የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ዋናው መለኪያ፣ በቅርፁ አገባብ ምክንያት የሚከሰተው መዋቅራዊ ለውጥ ነው፡፡ በ/አ-/ እና በ/አስ-/ ምክንያት፣ እንደ አስቴር ያለ፣ ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ ተሳቢ ይሆናል፣ ለባለቤትነት ደግሞ ሌላ ሀረግ አስፈልጎአል፡፡ ስለዚህም ካሳ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል፡፡ አንድ ቅርፅ እንደዚህ ያለ መዋቅራዊ ለውጥ የሚያስከትል ከሆነ፣ ጥገኛም ይሁን ነፃ፣ መዋቅራዊ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ቦታውም ከላይ እንደሚታየው የግስ ነው፡፡

ምሳሌ (34) አሻሚ ነው፡፡ አሻሚነቱ አስቴር በሚለው ስማዊ ሀረግ ማና ላይ ነው፡፡ ሀረጉ አድራጊ ወይም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ዕፀ መዋቅር (35) የሚያሳየው፣ ሀረጉ አድራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ ነው፡፡ ተደራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ፣ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም አስቴር ቡና እንዲፈላ እንድታደርግ ተደረገች የሚል ይሆናል፡፡ መዋቅሩም ተገብሮአዊ ነው፡፡ ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ በተራ ቁጥር (35) ከሚታየው ጋር አንድ ነው፡፡ አደረገ የሚለው ግስ ተ-ደረገ የሚል የተደራጊ አምድ ቅርፅ ይይዛል፡፡ /አሰ-/ ከሚለው አስደራጊ ምዕላድ ጋር ሲገናኝ፣ ግሱ /አስ-ተ-ድኧርርኧግ-/ የሚል ይሆናል፡፡ ቋንቋዋው የአስደራጊና የተደራጊ ምዕላድ ከትትሎሽን ስለማይፈቅድ፣ የተደራጊው ምዕላድ /-ተ-/ ይገደፋል፡፡ ይህ ሲሆን አስደረገ የሚለውን ላዕላይ ቅርፅ እናገኛለን፡፡ ይህ ቅርፅ ነው፣ አሻሚ የሆነው፡፡


ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ ደግሞ እንመልከት፡፡

ካሳ አስቴርን አስደባት 36

ይህ አረፍተ ነገር አሻሚ ነው፡፡ ከትርጉም አንፃር፣ አስቴር ሰዳቢ ወይም ተሰዳቢ ባለቤት ልትሆን ትችላለች፡፡ ርግጥ፣ በቅርፅ ደረጃ አስቴር የሚለው ስም /-ን/ የሚለውን የተሳቢ ምዕላድ ስላስከተለ፣ ተሳቢ ብሎም ተደራጊ ስም ነው፣

ይባል ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳዋያ ሲታሰብ፣ ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ የሚከተለው ይመስላል፡፡

37




ከዚህ ላይ ግሱ ሳቢ ስለሆነ፣ <u>አስቴር</u> የሚለውን ስም በተሳቢነት ይዞአል፡፡ ግሱ ተደራጊ ስለሆነና የባለቤቱ ቦታም ክፍት ስለሆነ፣ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ከተሳቢ ቦታው ተነስቶ ክፍት ወደሆነው የባለቤት ቦታ ይሄዳል፡፡ <u>ተሰደብ-</u> የሚለው ተደራጊ

ግስ /አስ-/ ከሚለው ምዕላድ ጋር ሲገናኝ /አስ-ተስደብ-አት/ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የአስደራጊው ምዕላድ /አስ-/ እና የተደራጊው (የተገብሮው) ምዕላድ /ተ-/ ሲከታተሉ፣ /ተ-/ ትገደፋለች፡፡ ባጭሩ የማንኛውም አስደራጊ አረፍተ ነገር ታህታይ ቅርፅ ገቢር ወይም ተገብሮ ሊሆን ይችላል፤ ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ የአሻሚነቱም ምክንያት ይኸው ነው፡፡

በግልፅ እንደሚታየው፣ የሞዩ ቦታ ክፍት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አረፍተ ነገሩ የ/አስ-/ መሙሊያ ሆኖ በሚገባበት ጊዜ ነው፡፡ አደረገ የሚለው መደበኛ (ነፃ) ግስ መሙሊያ ሆኖ ሲገባ፣ የሞዩ ቦታ እንድ[10] በሚለው ሞይ ይሸፈናል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው፡፡

[ካሳ [አስቴርን ሰው እንድትስድብ] አደረጋት] 38

ከዚህም ግሱ ቃላዊው አደረገ ሳይሆን፣ ምዕላዳዊው /አስ-/ በሚሆንበት ጊዜ፣ መሙሊያው አረፍተ ነገር ሞይ አይኖረውም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ቃላዊና ምዕላዳዊ ግሶችም በመሙሊያ አረፍተ ነገራቸው ይለያሉ፡፡ የምዕላዳዊ ግሶች መሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውምና፡፡

በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ይኸው አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ የዚሁ አቃፊ አረፍተ ነገር ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[አስቴር [--- ሰው እንድትስድብ] ተደረገች] 39

አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ መስረታዊ (ታህታይ) ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው፡፡ ይህም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ ነው፡፡ ከዚህ ቦታ ተነስቶ ወደ አቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በመውጣት [ሰው እንድትስድብ ተደረገች] ለሚለው ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ሊሆን ችሏል፡፡ ይህ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል፣ ይመስላል ስለሚለው ግስ ባህሪ ስንወያይ ያስተዋልነውን ሊያስታውሰን ይገባል፡፡ ያኔ የአንድ አቅፍ አረፍተ ነገር ባለቤት

---

[10] ሞዩ እንድ የሚሆነው፣ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ግስ የካልዓይ እንቀፅ ሲሆን ነው፡፡ ግሱ የቀዳማይ እንቀፅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሞዩ እንደ ይሆናል፡፡ ምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ብርጭቆ እንደ ሰበረ ሰማሁ

(ለ) ካሳ ብርጭቆ እንዲሰብር (/እንደ-/ይ-ስእብር/) አዘዝኩ

የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤትም ሊሆን እንደሚችል አይተን ነበር፡፡ ከዚህ ላይ የምናየውም ይህንኑ ሁኔታ ነው፡፡

ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) [---[አስቴር ቡና እንድታፈላ] ይደረጋል (/ይ-ት-ድኧርርኧግ-ኣልል/)] 40
[ይድድኧርርኧግኣልል]

(ለ) [አስቴር]---ቡና እንዲታፈላ] ትደረጋለች (/ት-ት-ድኧርርኧግ-ኣልል-ኧች/)]
[ትእድድኧርርኧግኣልልኧች]

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ይደረጋል የሚለው የተገብሮ ግስ ባለቤት በግሀድ አይታይም፡፡ /ይ-/ ከሚለው አፀፋ ብቻ ስስተኛ መደብ መሆኑን መለየት ይቻላል፡፡ በግሀድ የማይከሰተው፣ ባለቤቱ መደበኛ ተውላጠ ስም ሳይሆን፣ ቀደም ሲል የይስሙላ ባለቤት ያልነው፣ it የሚለው ተውላጠ ስም በመሆኑ ነው፡፡ በአማርኛ፣ ይህ ተውላጠ ስም መደበኛ ቅርፅ እንደሌለውና ከላይ እንደሚታየው፣ በአፀፋ ብቻ እንደሚጠቀስ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ባለቤት ሆኖ የሚገባውም እንደ ይመስላል ላለ የሁኔታ ግስ እና እንደ ይደረጋል (ይ-ት-ደረጋል) ላሉ ተደራጊ ግሶች ነው፡፡

እንደነዚህ ያሉ ግሶች መሰረታዊ ባህሪ አድራጊ ባለቤት አለመፈለግ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ የነዚህ ግሶች ባለቤት ቦታ ክፍት (-) ይሆናል፡፡ በላዕላይ መዋቅር፣ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤት የግድ ማግኘት አለባቸው፡፡ በቅርፃቸው ሙሉ ሆነው መገኘት አለባቸውና፡፡ ባለቤት ሊሆን የሚችለው ደግሞ አንድም የይስሙላው ተውላጠ ስም፣ ማለትም it ፣ አለያም የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የሆነው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የይስሙላው ተውላጠ ስም ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ምሳሌ 40(ሀ)ን እናገኛለን፡፡ የዚህ አረፍተ ነገር ግስም ይደረጋል የሚል ነው፡፡ የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ 40(ለ)ን እናገኛለን፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ፣ ግሱ ት-ደረጋለ-ች ይሆናል፡፡ ግሱ የስስተኛ መደብ፣ አንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆኑትን /ት-/ እና /-ች/ን ያሳያል፡፡ ከዚህም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ በርግጥ አስቴር የሚለው የስስተኛ መደብና የአንስታይ ፆታ ስም መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን ዋናው ጉዳይ፣ በተደራጊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ ባለቤት ስማዊ ሀረግም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል ስለ ተራ ተደራጊ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ በታህታይ መዋቅር ተሳቢ የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ በላዕላይ መዋቅር ባለቤት ሲሆን አይተናል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታየው ግን በተራ

አረፍተ ነገሮች መዋቅር ነው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ ውስብስብ ሲሆኑ፣ የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የነበረው ስማዊ ሀረግ የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ይሆናል፡፡ እንደ አቃፊው ግስ አይነትም፣ ባለቤቱ አድራጊ ወይም ተደራጊ ይሆናል፡፡ ተደራጊ የሚሆነው በምሳሌ 40(ለ) እንደሚታየው፣ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

ስለ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን፡፡ ግሶች አረፍተ ነገራዊ ከሆነ መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ (ግላጭ) ጋር ሲዋቀሩ፣ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግን ይመሰርታሉ፡፡ መሙሊያው እና/ወይም አጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ወይም ስማዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ግሳዊ አረፍተ ነገር ምን ጊዜም ውሱን ነው፡፡ የባለቤት፣ የተሳቢ ወይም የመሰተዋድድ አፀፋ ይኖረዋል፡፡ እንደ /-አልል/ ያለ ጊዜን የሚያመለክት ምዕላድም ይኖረዋል፡፡ ስማዊ ከሆነ ውሱን ወይም ኢውሱን ሊሆን ይችላል፡፡ ውሱን ስማዊ አረፍተ ነገር ባለቤቱን ብቻ የሚጠቁም አፀፋ ይኖረዋል፡፡ ጊዜን የሚያሳይ ምዕላድ ግን አይኖረውም፡፡ ጊዜው የሚወሰነው በአቃፊው አረፍተ ነገር የጊዜ አይነት ነው፡፡

የግሳዊ ሀረግ የውስብስብነት ደረጃ እንደ መሙሊያው እና/ወይም አጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ ይለያያል፡፡ የመሙሊያው እና/ወይም የአጎላማሹ አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ ውስብስብ ከሆነ፣ ዋናው ግሳዊ ሀረግ በጣም ውስብስብ ይሆናል፡፡ ከእንደዚህ አይነት ግሳዊ ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ውስብስብ ይሆናል፡፡

የግሳዊ ሀረግ መሪ ቃላዊ ወይም ምዕላዳዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ምዕላዳዊ የሚሆነው ግሳዊ ሀረጉ አስደራጊ ሲሆን ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ሀረጉ /አ-/ ወይም /አስ-/ በሚሰው አስደራጊ ምዕላድ መሪነት ይዋቀራል፡፡ በነዚህ መሪነት የሚዋቀረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መሙሊያ አረፍተ ነገራዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሞይ የለውም፡፡ በቃላዊ ግስ መሪነት የሚዋቀር ንዑስ ግሳዊ ሀረግ፣ አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ፣ ሞይ አለው፡፡ ሞዩም <u>እንደ</u> የሚለው ምዕላድ ነው፡፡ አስደራጊ ግሳዊ ሀረግ በአድራጊ ወይም በተደራጊ ግስ መሪነት ሊዋቀር ይችላል፡፡ የተደራጊ ምዕላድዋ ከአስደራጊው ምዕላድ ቀጥላ ስትገባ ትገደፋለች፡፡ በዚህ ምክንያት ሀረጉ አሻሚ ይሆናል፡፡ አሻሚነቱን ለማስወገድ በአስደራጊው ምዕላድ፣ ማለትም በ/አስ-/ ፋንታ <u>አደረገ</u> የሚለውን ቃላዊ አስደራጊ ግስ መተካት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆን የተደራጊዋ ምዕላድ የሆነችው /ተ-/ በግሀድ ትታያለች፣ እናም አስደራጊው ግሳዊ ሀረግ ተደራጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ወደሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እንሂድ፡፡